ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

# የግብርና ምርት ውል ትግበራ መመሪያ
## (ቴክኒካል ጋይድላይን)



2015 ዓ/ም

# የግብርና ምርት ውል ትግበራ መመሪያ

## (ቴክኒካል ጋይድላይን)


አዘጋጅ

ግብርና ሚኒስቴር

የግብርና ኢንቨስትምንትና ግብዓት ዘርፍ

የግብርና ኢንቨስትመንትና ምርት ግብይት ዋና ስራ አስፈፃሚ

## ምስጋና

ይህ የግብርና ምርት ውል ትግበራ መመሪያ (ቴክኒካል ጋይድላይን) ወደ ስኬታማ ሕትመት እንዲመጣ ጉልህ አስተዋጽኦ ላደረጉ አጋር ተቋማት ሁሉ ልባዊ አድናቆትን እያቀረብን በተለይም GIZ፣ ATI እና Techno Serve Ethiopia የመሳሰሉ የልማት አጋሮች በመመሪያው ዝግጅት እና የህትመት ሂደት ሁሉ በጀታቸው እና በዋጋ ሊተመን የማይችል ምክራቸውን በመለገስ ስላደረጉልን አስተዋጽኦ ከልብ እናመሰግናለን።

በተጨማሪም ይኽ ቴክኒካል መመሪያ ወደ ስኬታማ ሕትመት እንዲመጣ ጉልህ አስተዋጽኦ ላደረጉ፣ጊዜያቸውንና እውቀታቸውን ላበረከቱልን ግለሰቦች ምስጋናችን ከፍ ያለ ነው።

**ማውጫ** **ገጽ**

1. መግቢያ..........3
2. ዓላማ..........4
2.1.ዋና ዓላማ..........4
2.2. ዝርዝር ዓላማ..........4
የቴክኒካል ጋይድላይኑ አስፈላጊነት..........4
የአዘገጃጀት ስልት..........5
4.1.የመጀመሪያ ደረጃ ጥሬ ሀቅ (Primary Data)..........5
4.2.የሁለተኛ ደረጃ ጥሬ ሀቅ (Secondary Data)..........5
የሚጠበቅ ውጤት..........6
6.የግብርና ምርት ውል የአሰራር ትንተና..........6
6.1.የግብርና ምርት ውል አለም አቀፍ ትንተና..........6
6.2.የግብርና ምርት ውል አሰራር ሀገራዊ ገጽታ..........7
7.የግብርና ምርት ውል መገለጫ..........10
7.1.የግብርና ምርት ውል ትርጉም እና ምንነት..........10
7.2. የግብርና ምርት ውል ጠቀሜታና ውስንነት..........11
7.2.1. የግብርና ምርት ውል ጠቀሜታ..........11
7.2.2. የግብርና ምርት ውል ውስንነቶች..........13
7.3. በአምራችና አስመራች መካከል ሊኖሩ የሚችሉ የግብርና ምርት ውል ዓይነቶች (ሞዴሎች)..........14
7.3.1. የተቀናጀ ውል ሞዴል (Nucleus State Model)..........14
7.3.2. የተማከለ ውል (Centeralized model)..........15
7.3.3. በርካታ ተዋናዮች የሚሳተፉበት የግብርና ምርት ውል ሞዴል ( Multipartite)..........15
7.3.4. አገናኝ ሞዴል (Intermediary model)..........16
7.3.5. መደበኛ ያልሆነ ውል (Informal Model)፡-..........16
8.የግብርና ምርት ውል ቅድመ ዝግጅቶች..........16
8.1.ትስስሩ የሚካሄድበት አካባቢ ማወቅና መለየት..........16
8.2.የግብርና ምርት ዓይነት እና መጠንን አስቀድሞ መወሰን..........17
8.3.በሀገሪቱ የግብርና ምርት ውልን የሚያበረታታ የህግ ማዕቀፍ መኖሩን እና

ተፈፃሚነቱን ማረጋገጥ.....17
9.የግብርናምርት ውል አሰራር ስርዓት አደረጃጀት.....17
10.የግብርናምርት ውል ስምምነት ሰነድ አዘገጃጀትና አጠቃቀም.....19
11.የምልመላ መስፈርት.....20
11.1.የአስመራች መመልመያ መስፈርት.....21
11.2.የአምራች መመልመያ መስፈርት.....21
12.የፈጻሚዎችና ባለድርሻ አካላት የስራ ድርሻ.....22
12.1.የግብርና ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት.....22
12.2.የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተግባርና ኃሊፊነት.....23
12.3.የህብረት ስራ ኮሚሽን ሚና.....23
12.4.መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሚና.....24
12.5.የክልል ግብርና ቢሮ.....24
12.6.የወረዳ ግብርና ጽ/ቤት.....25
13.የክትትል፣ ድጋፍና መማማር ሥርዓት.....27
13.1.ምርታመነትን እና የምርት ጥራትን መከታተል.....27
13.2.የሰው ሃብት ክትትል.....27
ዋቢ መጻህፍት/ሰነዶች.....29

## 1. መግቢያ

መንግስት የግብርና ምርት ጥራት፣ የአመራረት ቅልጥፍናና ተወዳዳሪነት እንዲሁም የግብርና እና አግሮ-ኢንዱስትሪ ተመጋጋቢነት በማሳደግ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እውን ለማድረግ የግብርና አምራቾች ገበያ ተኮር ምርቶችን ወደ ማምረት እንዲሸጋገሩ በማድረግ ምርትን ከሚያዘጋጁ፣ ከሚያቀነባብሩ እና ሌሎች እሴት ከሚጨምሩ አግሮ ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም ከትላልቅ ገዥዎች ጋር ቀጣይነት ያለው ትስስር ለመፍጠር የአምራች-አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን ህጋዊ ማዕቀፎችን ማለትም በቁጥር 1289/2015 በወጣው አዋጅ እንዲሁም የአዋጁ ማስፈጸሚያ መመሪያ እና ደንብ እንደተዘጋጀ ይታወቃል፡፡

በእውቀትና በክህሎት እንዲሁም በህግ ማዕቀፍ የሚመራ የግብርና ምርት ውል ትግበራ  የግብርና ምርት ለማስተዋወቅና ከግብይት ጋር ለማስተሳሰር የሚያስችል ውጤታማ መንገድ ነው፡፡ የግብርና ምርት ውል ምርትን ከግብይት ጋር የሚያገናኝ ድልድይ ቢሆንም በእውቀትና በመደራደር ችሎታቸው እኩል ባልሆኑ ወገኖች መካከል የሚፈፀም የውል ስምምነትም ነው፡፡ ይኸንን ስንልም ኩባንያዎች፣የመንግስት አካላት ወይም ግለሰብ እና ሥራ ፈጣሪዎች በአንድ በኩል እንዲሁም  የኢኮኖሚና የድርድር ውስንነት ያላቸው አርሶ/አርብቶ አደሮች በሌላ በኩል የሚሰለፉበት አውድ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይሁን እንጂ ስምምነቱ የእውቀት፣የድርድርና የኢኮኖሚ ልዩነት ባላቸው አካላት የሚደረግ ስምምነት ቢሆንም  ለአርሶ/አርብቶ አደሮች ወይም ለአምራቾች ገቢ መጨመር እና ለአስመራቾች ከፍተኛ ትርፋማነት አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚችል የማምረትና

የመገበያየት ማነቆዎችን የሚፈታ ሳይንሳዊ ጥበብ ነው፡፡ እንደ ሀገር ስናይ በዚህ ሳይንሳዊ ጥበብ ላይ የሚታየው ዋነኛ ችግር ስለ ግብርና ምርት ውል ውስብስብነት እና እንዴት በተሳካ ሁኔታ ማስተዳደር እንደሚቻል የእውቀት እጥረት በሁሉም ተዋናዮች ዘንድ መኖሩ ነው፡፡ ይህንን ችግር ሲውል ሲያድር ደካማ አፈጻጸምን፣ በመጨረሻም ሀገራዊ ውድቀትን ሊያስከትል የሚችል ነው፡፡

ስለዚህ በሀገራችን ያለውን የግብርና ምርት ውል ስኬታማ ለማድረግ ጥንቃቄ የተሞላበት አመራር እና ዝግጅት የሚያስፈልገው መሆኑን በመገንዘብ ትግበራውን ህጋዊ ማዕቀፍን የተላበሰ እንዲሁም በቴክኒካል ጋይድ ላይን የታገዘ የስራ ባህል መመስረት አስፈላጊ ነው፡፡ በእውቀትና በክህሎት ላይ የተመሰረተ እና በየደረጃው ወጥነት ያለው የግብርና ምርት ውል ለመከወን የሚያስችለንን የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት ሲባል ይህንን የግብርና ምርት ውል የትግበራ መመሪያ (ቴክኒካል ጋይድላይን) በዚህ መልኩ ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡

## 2. ዓላማ

### 2.1. ዋና ዓላማ

የግብርና ምርት ውል አተገባበርን በማዘመን፤ በአምራችና በአስመራች መካከል ያለውን መተማመን በማጠናከር እና ዘለቄታዊ ትስስር በመፍጠር ላይ ተመስርቶ በግብርና ምርት ውል ትግበራ ላይ ተሳትፎ ባላቸው በሁሉም ተዋንያን መካከል ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን መዘርጋት፡፡

### 2.2. ዝርዝር ዓላማ

- ✓ በግብርና ምርት ውል አሰራር ለሚሳተፉ ተዋንያኖች የአሰራር ግልጽነትን ለመፍጠርና ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ
- ✓ በግብርና ምርት ውል ተዋናዮች ዘንድ የስራ ድርሻ፣ተናባቢነትንና ዘላቂ አሰራርን ማስፈን፡፡
- ✓ በሀገራችን ያለውን በግብርና ምርት ውል ለሚከውን የአምራችና የአስመራች የግብይት ሰንሰለት ቀልጣፋ፣ ቀጣይነት ያለው እና አስተማማኝ እንዲሆን ማድረግ፡፡
- ✓ የግብርና ምርት ውል አሰራር ስርዓትን በዘመናዊ መንገድ ዲጂታላይዝ ለማድረግና የመረጃ ተደራሽነትን ማረጋገጥ

## 3. የቴክኒካል ጋይድላይኑ አስፈላጊነት

ይህ የግብርና ምርት ውል ማስፈጸሚያ የትግበራ መመሪያ ማዘጋጀት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን የሚከተሉት ነጥቦች በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡

- ✓ የግብርና ምርት ውል አስመልክቶ የወጡ አዋጅ፣ደንብና መመሪያን ተግባራዊ ለማድረግ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር፣
- ✓ በግብርና ምርት ውል የሚሳተፉ አምራችና አስመራች ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርት በግልጽ ስለሚያስቀምጥ ለቀጣይ አሰራር አቅጣጫ ሰጪ በመሆኑ፣
- ✓ እንደሀገር ያለውን የግብርና ምርት ውል አተገባበር ወጥ የሆነ አሰራር እንዲኖር ለማስቻል፣

- ✓ የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት በማስቀመጥ ቀጣይ ቅንጅታዊ አሰራርን ለማስፈን፤
- ✓ ቀልጣፋ፣ ግልጽ እና ተጠያቂነት ያለው የግብርና ምርት ውል አሰራር እንዲኖር ለማስቻል፤
- ✓ በየደረጃው ያሉ ተዋንያንና ባለድርሻ አካላት አቅም ለመገንባት እንደ ስልጠና. ማኑዋል የሚያገለግል በመሆኑ፣
- ✓ የአምራችና አስመራች ተሳትፎ ለማሳደግ እና የጋራ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፤

በአጠቃላይ የትግበራ መመሪያ ዝግጅት አስፈላጊነት አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች/አርብቶ አደሮች በሚያመርቱት ምርት የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ ምርትና ምርታማነት የሚያሳድጉ ዘመናዊ የግብርና ዘዴ ተግባራዊ በማድረግ ጥራቱን የተጠበቀ የግብርና ምርት እንዲያመርቱ፣በአቅራቢያቸው ከሚገኙ አልሚ ባለሀብቶች ጋር የግብርና ምርት ውል ትስስር እንዲፈጥሩ እና ቀጣይነት ያለው እድገት በማስመዝገብ ኑሯቸው እንዲሻሻል ማድረግ ነው። በተጨማሪም በዘርፉ የተሰማሩና መሰማራት ለሚሹ አርሶ/አርብቶ አደሮች ኩባንያዎች፣ ኢንተርፕራይዞች፣ ወጣቶችና ሴቶች፣ እና ሌሎችም በተነደፈው ስልት ወይም መመርያ እየተጠቀሙ ቀጣይነት ያለው እና ትርፋማነትን የሚያረጋግጡ አሰራሮችን መከተልና መተግበር ያስፈልጋል። እንደ ሀገር የሚናበብ አሰራር ለመዘርጋት ደግሞ የጋራ መርህ መንደፍ በማስፈለጉ ይህ የግብርና ምርት ውል የቴክኒካል ጋይድላይን ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡ ፡

## 4. የአዘገጃጀት ስልት

ይህ የግብርና ምርት ውል ትግበራ መመሪያ/ቴክኒካል ጋይድላይን ሲዘጋጅ የሚከተሉትን ስልቶች ጥቅም ላይ ውሰዋል፡-

### 4.1. የመጀመሪያ ደረጃ ጥሬ ሀቅ (Primary Data)

የግብርና ምርት ውል አሰራርን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጥረት እያደረጉ ያሉና የሚመለከታቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እንዲሁም ኢንተርፕራይዞች/ኮርፖሬሽኖች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የአሰራራቸውን ተሞክሮ ለመቅሰም የሚያስችሉ ቃለ-መጠይቆችን፣ የመስክ ጉብኝትን፣ የቡድን ውይይት በመጠቀም የመጀመሪያ ደረጃ ጥሬ ሀቅ መረጃዎችን በመሰብሰብ በግብዓትነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

### 4.2. ከተላያዩ ጽሑፎችና መዛግብት የተገኘ መረጃ (Secondary Data)

በተለያዩ አካላት በግብርና ምርት ውል ዙሪያ ያጠኗቸው ጥናቶችን በማጣቀሻነት በመጠቀም፣ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጠንተው በተለያዩ ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ደረጃ የታተሙ የህትመት ውጤቶች በተለያዩ በይነ መረብ የተገኙ የተረጋገጠላቸው የጥናት ውጤቶች ግብዓትነት በመጠቀም ይህንን የትግበራ መመሪያ (ቴክኒካል ጋይድላይን) ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡

## 5. የሚጠበቅ ውጤት

ይህ የግብርና ምርት ውል ቴክኒካል ጋይድላይን በግብርና ሚኒስቴር ማኔጀመንት(የአስተዳደር) አካላት ጸድቆ በየደረጃው ባሉ የሀገሪቱ የግብርና ምርት ውል አስፈፃሚ ተቋማት ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን የሚከተሉትን ዋና

ዋና ውጤቶችን እንደሚያስገኝ ይታመንበታል።

- ✓ እንደሀገር የተዘረጋ ወጥ የሆነ (ተቀራራቢ የግብርና ምርት ውል አፈፃጸም)፣
- ✓ በዘርፉ መሰማራት የሚፈልጉ አምራችና አስመራችን ለመመልመል የሚያስችል ግልጽና የማያሻማ የምልመላ መስፈርት፣
- ✓ ሚናቸው በግልፅ የተቀመጠ በግብርና ምርት ውል የተሰማሩ ተዋናዮችን የሚደግፉ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣
- ✓ በባለቤትንት ስሜት የግብርና ምርት ውል አፈፃጸምን ለመደገፍ የተፈጠረ አቅም፤
- ✓ ዲጂታላይዝድ፣ ቀልጣፋ እና ግልጽነት ያለው የግብርና ምርት ውል አሰራር፣
- ✓ ወቅታዊና ተደራሽ የሆነ ጥራት ያለው የመረጃ ልውውጥ እና ለሚያጋጥሙ የአፈፃጸም ተግዳሮት ፈጣን ምላሽ ናቸው።

# 6. የግብርና ምርት ውል የአሰራር ትንተና

## 6.1. የግብርና ምርት ውል አለም አቀፍ ትንተና

እንደ ዓለም አቀፉ የልማት ድርጅት ሪፖርት (2008) በግብርና ምርት ውል ትስስር ስምምንት ውስጥ ሁለቱም ተዋናዮች (አምራቹና አስመራቹ) በዋናነት አምራቹ በይበልጥ ተጠቃሚ እንደሚሆንና የግብርና ምርት ውልን በአግባቡ መደገፍ ከተቻለ የአንድን ሀገር ድህነት ለመቀነስ ከፍተኛ ድርሻ ሊወጣ እንደሚችል ያትታል። በዘመናዊ የግብርና ውል አሰራር ህንድ ቀዳሚ ሀገር ስትሆን ይህም በአስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተለያዩ ሰብሎች (በጥጥ፣

ትምባሆ እና  የንግድ ሰብሎች) ላይ ትኩረት በማድረግ ይሰራ ነበር። ከነጻነት በኂላም  በዘር ማምረት እና በሸንኮራ አገዳ (ከ1960ዎቹ)፣ ወተት (ከ1970ዎቹ)፣ ቲማቲም  (በ1980ዎቹ)  በስፋት ይሰራ ነበር። በቻይናም ከ1 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን  ጀምሮ እየተሰራበት እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ፣

ይህን እውነት ቀድመው በመረዳት በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች ዘርፉን በአግባቡ ለመደገፍ የሚያስችል መንግስታዊ አደረጃጀት ፈጥረው እየተንቀሳቀሱ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ለመጥቀስ ያህል በብራዚል የዶሮ ርባታ ምርት 70 በመቶ፣ በቬትናም የጥጥ ምርትና ወተት አቅርቦት 90 በመቶ፣ ኬኒያ የሸንኮራ አገዳ  እና የሻይ ቅጠል ምርት 60 በመቶ፣ ጥጥና ትንባሆ 100 % አቅርቦት በግብርና ምርት ውል ከተሰማሩ አካላት እንደሚገኝ ጥናቶች በግልጽ  ያሳያሉ። ዓለም አቀፍ ልምዶች የሚያሳዩት በአዳጊ ሀገራት በዋናነትም በአፍሪካ የግብርና ምርት ውል የሚከተሉት ችግሮች እንደገጠሙት ያሳያል፤ ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፡ -

- ✓ የመንግስት የድጋፍ ቁርጠኝነት አለመኖር፣
- ✓ በአስመራች ድርጅቶች በኩል ካፒታል እጥረት መኖር፣
- ✓ በአስመራቹ በኩል የተጠናከረ የቁጥጥር ሥርዓት ያለመኖር፣
- ✓ አለመግባባቶች ለመፍታት የሕግ አተገባበሩ አዝጋሚ መሆን፣
- ✓ ገበያ ተኮር የሆነ የምርምር ውጤት አለመኖር፣
- ✓ በአስመራችና አምራች ዘንድ የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር፣
- ✓ የብድር አገልግሎትና የግብዓት አቅርቦት ችግር፣

✓ ጠንካራ የሆነ የቴክኒክና የኤክስቴንሽን አገልግሎት አለመኖር፣

✓ በግብርና ውል ዋጋ ተመን በምርት ጥራት ደረጃ አወጣጥ እና በአስተሻሸግ ላይ በአምራችና አስመራች መካከል ግልፅነት ያለመኖር፣

✓ በምርት ዋጋ መዋዥቅ ምክንያት የጎንዮሽ ሽያጭ መከሰት በዋናነት እንደ ችግር ተለይተዋል፡፡

### 6.2. የግብርና ምርት ውል አሰራር ሀገራዊ ገጽታ

በኢትዮጵያ የግብርና ምርት ውል አሰራር ረዥም እድሜ እንዳለው መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ እንደማሳያም፡-

❖ <u>የትንባሆ እፀዋት አስመራቾች፡-</u> እ.ኤ.አ.1947 ጀምሮ በሻሸመኔ፣ በሃዋሳ፣ በሸዋ ሮቢትና በወላይታ አካባቢ ያሉ አነስተኛ አርሶ አደሮች በማሳቸው ላይ በሚያበቅሉት የትንባሆ እፅዋት በባህልዊ መንገድ ለአካባቢው ገበያ ከሚጠቀሙበት በላይ በሀገሪቱ በብቸኝነት ለተቋቋመው የኢትዮጵያ ሲጋራ ፋብሪካ በጥሬ እቃነት በውል ግብርና ሲያቀርቡ እንደነበረና እስካሁንም ባለው አሰራር እየተጠቀሙ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

❖ <u>በወንጂ አካባቢ ሸንኮራ አገዳ አብቃይ አርሶ አደሮች፡-</u> እ.ኤ.አ.1960ዎቹ ጀምሮ በአካባቢው ብቸኛ በሆነው ስኳር ፋብሪካ የሸንኮራ አገዳ ምርት በማቅረብ በግብርና ምርት ውል አሰራር መጠቀም እነደጀመሩና እስከአሁንም በሀገሪቱ እየተስፋፉ ባለባቸው የስኳር ፋብሪካዎች በየአካባቢው ፋብሪካው ከያዘው የሸንኮራ አገዳ ማምረቻ መሬት ውጪ በአካባቢው አርሶ አደሮች ጋር የግብርና ምርት ውል በመያዝና አስፈላጊ ግብዓቶችን (እንደ ሸንኮራ አገዳ ዝርያና የትራክተር እርሻ፣ የመሳሰሉት) በማቅረብ አምራች እና

አስመራች በሚያደርጉት የገበያ ትስስር ከመጠቀማቸውም በላይ ለሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ ከፍተኛ አስታውፆ እያበረከተ ይገኛል፡፡

❖ <u>የሻይ ልማት ተሳታፊ አርሶ አደሮች፡-</u> በኢትዮጵያ ከፍተኛ ደጋማ እና ወይና ደጋ አካባቢዎች ለሻይ ተክል ተስማሚ የአየር ሁኔታ እና የአፈር ዓይነት በመኖሩ ጥራት ያለው ሻይ ለውጭ እና ለአገር ውስጥ ፍጆታ በተለያዩ ባለሀብቶች እየለማ ያለው የሻይ ተክል በተለይም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና በኦሮሚያ ክልሎች የኢትዮ-አግሪ-ሴፍት ኃ/የተ/የግ/ማህበር (ውሽውሽ እና ጉሜሮ ሻይ ልማት) እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በሚገኙ የምስራቅ አፍሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር (ቸዋካ ሻይ ልማት) ከሚያለሙት መሬት በተጨማሪም የአካባቢው አነስተኛ ማሳ ያላቸው አርሶ አደሮች መሬት ላይ ሻይ በማልማት ላይ ይገኛሉ፡፡ አነስተኛ ማሳ ያላቸው አርሶ አደሮች በማህበር ተደራጅተው አረንጓዴ ቅጠሎችን በማምረት በግብርና ምርት ውል የግብይት ስርዓት በመተግበር ለኩባንያዎቹ እንዲያቀርቡ ተደርጓል እየተደረገም ነው፡፡ በዚህም የአሰራር ስርዓት ከአምራችና አስመራች ጥቅማጥቅም በዘለለ ለሀገር የውጪ ምንዛሪ ምንጭ በመሆን በፋብሪካ ሂደታቸውን ጨርሰው ወደውጭ ከምንልካቸው ጥራታቸውን የጠበቁ የግብርና ምርት አንዱ ለመሆን በቅቷል፡፡

❖ <u>የቢራ ገብስ ግብይት፡</u> የአሰላ ብቅል ፋብሪካ ደጋማ በሆኑ የሀገሪቱ ስነ ህዳራት የቢራ ገብስ አምራች አርሶ አደሮችን በማደራጀትና ድጋፍ በመስጠት ብሎም ምርታቸውን ካለው የገበያ ዋጋ ከፍ ባለ ሁኔታ

ለመግዛት ውል በማስገባት በቂ ግብዓት ለፋብሪካው ማግኘት ከመቻሉም ባሻገር ለቢራ ገብስ ግዥ የሚውል የውጭ ምንዛሪ በማስቀረት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅዖ እያበረከተ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ እንደግለሰብም ሆነ አደረጃጀት በመፍጠር በተለመዱ አሰራሮችም ይሁን በነበሩት የሀገሪቱ የፍትሐብሄር ህግ እየተመራ የሕብረት ሥራ ዩኒየኖች፣ ኃ/የተ/የግል ኩባንያዎች፣ አክሲዮን ማህበር፣ ኤክስፖርተሮች እና ሌሎችም የተሳተፉበት የግብርና ምርት ውል በግብርና ምርቶች ላይ በተለይም በእንስሳት ልማት ንዑስ ዘርፍ (ጥሬ ውተት ማሰባሰብ፣ ንብ ማነብ፣ ዶሮ እርባታ እና የተለያዩ እንስሳት ማድለብ) በሰብል ልማት ንዑስ ዘርፍ (በተለያዩ የእህል ዓይነቶች፣ ምርጥ ዘር ማምረት፣ የቢራ ገብስ ልማት፣ አኩሪ አተር፣ ኤክስፖርቴብል የግብርና ምርቶች፣ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት (አቮካዶ፣ አትክልቶች) እየተተገበረ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

እንደሀገር የግብርና ምርት ውል አሰራር ረዥም እድሜ ቢኖረውም በአፈጻፀም ላይ በርካታ ችግሮች እየገጠሙት እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ለዚህም አንዱ መንስኤ መንግስት አደረጃጀት ፈጥሮ እስካሁን እንዳልሔደበት እና በዚህም ምክንያት እንደ ሀገር ከዘርፉ ሀገራችን መጠቀም የሚገባትን ያክል መጠቀም አለመቻሏ ነው፡፡ መንግስትም ይህን እውነት ተረድቶ በአሁኑ ሰዓት አደረጃጀት ፈጥሮ ዘርፉን ለመደገፍ ጥረት እያደረገ ቢሆንም በአፈጻጸም ወቅት በአስመራችና በአምራቹ እየገጠሙ ያሉ ዋና ዋና ችግሮችም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## ❖ በአስመራቹ

- ✓ ጠንካራ አቅም እና ግንዛቤ ሳይኖራቸው በግብርና ምርት ውል ላይ መሰማራታቸው፤
- ✓ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት አለመቻሉ፤
- ✓ ትስስር ፈጥረው እየሰሩ ላሉ አምራቾች በቂ ድጋፍ ማድረግ አለመቻላቸው፤
- ✓ ምርቱ ከተሰባሰበ በኋላ በወቅቱ ክፍያ አለመፈፀሙ፤
- ✓ በስፋት ወደ ዘርፉ የመግባት ፍላጎት ማጣት ወዘተ ይጠቀሳሉ።

## ❖ አምራቹ

- ✓ የሚሰጠውን የስልጠና ድጋፍና የሙያ ምክር ተከትሎ ያለመስራት፤
- ✓ ጉዳዩ በማይመለከታቸው አካላት የተነሳ ውል ገብተው ያመረቱትን ምርት ለአስመራች ያለማቅረብና የውል ተገዥ ያለመሆን፤ የተረጋጋ የምርት ዋጋ አለመኖር፤
- ✓ በብድር የወሰዱትን ግብዓት ዋጋ በስምምነታቸው መሰረት አለመፈፀም/ አለመክፈል ወይም አለመመለስ፣
- ✓ ከግንዛቤ ማነስ የተነሳ አስመራቹን እንደ እርዳታ ተቋም መቁጠር፣
- ✓ በተፈለገው ስታዳርድ መሰረት ምርቱ ጥራቱን የጠበቀ አለመሆን፤
- ✓ እንደ ምርቱና አመራረቱ ባህሪ በዋጋ ተመን እና የምርት ጥራት አወሳሰን ግልጽነት ማጣት (የዋጋ ተመን ወጥና ከተከላ በፊት መሆኑ)፤
- ✓ እንደሌሎች ምርቶች ዓለምአቀፋዊና ሀገራዊ የሆነ የዋጋ ተመን አሰራር አለመኖሩ፤

- ✓ አንዳንድ የግብርና ምርት አማራጭ ገበያ ባለመኖሩ በዋጋ አተማመን አምራች ለመዳራደር አለመቻል፤
- ✓ በአምራችና አስመራች የመተማመን አቅም ያለመዳበር
- ✓ የአመራረት ሂደታቸው ረጅም ጊዜ ለሚወስዱ የግብርና ምርት አይነቶች አርሶአደሩን ተጠራጣሪ እንዲሆንና ሌሎች በአጭር ጊዜ ሊደርሱ በሚችሉ አትክልቶች ማተኮሩ የግብርና ውል ሥርዓቱ እንዳይቀጥል እንቅፋት ፈጥሯል።

## 7. የግብርና ምርት ውል መገለጫ

### 7.1. የግብርና ምርት ውል ትርጉም እና ምንነት

እንደ ዓለም አቀፍ የምግብና የእርሻ ድርጅት ገለጻ "የግብርና ምርት ውል" ማለት በአምራቹ እና በአስመራቹ መካከል የሚኖር የግብርና ምርት አመራረት ሒደትና የተመረተው ምርት ለገዥው ወይም ለአስመራቹ የሚቀርብበት ስምምንት ሲሆን በሒደቱ ሁለቱም ወገኖች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ስርአት እንደሆነ ይገልጻል።

በአምራችና አስመራች ግንኙነት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1289/2015 "የግብርና ምርት ውል ማለት በግብርና ምርት አምራች እና በአስመራች መካከል የሚደረግ የስምምነት ሰነድ ነው።" በሌላ አባባል በግብርና ምርት ውል የተሰማሩ አምራችና አስመራች መካከል የሚኖር ስምምነት ሲሆን አምራቹ የተለያዩ የግብርና ምርቶችን በመጠንና በጥራት አምርቶ ውል ለገባለት አስመራች የሚሸጥበት ሂደት ነው። በተጨማሪም ምርቱን የሚገዛው አስመራች ደግሞ ለአምራቹ የምርት ጥራትና መጠንን በሚፈልገው ሁኔታ ሊጨምርለት የሚችል ግብአት፤

ብድር፤ ሙያዊ ምክር እና የግብይት አገልግሎቶቹን ለአምራች የሚያቀርቡበት ሥርዓት ነው። በግብርና ምርት ውል ሂደት ውስጥ አምራቹ ምርቶቹን ለአስመራች በመሸጥ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሚታቸውን በጋራ የሚያጎለብቱበት ስርአት ነው።

በዚህ ተግባር ላይ የተሰማራ አስመራች ወደውጭ በስፋት ለመላክ በመጠንና በጥራት የሚያስፈልጋቸውን ያህል ምርት እንዲመረትላቸው ለማድረግ ከአርሶ አደሮች ጋር የንግድ ምክክር ያደርጋሉ፣ በተጨማሪም ምርቱ ተከታታይ እንዲሆንላቸው ለማስቻል በባለሙያዎቻቸው አማካኝነት ለአምራቹ የተለያዩ የምክር፣ የስልጠና የግብአት እና ሌሎች ድጋፎችን እንደሚሰጡ የተለያዩ ሀገሮች (ዛምቢያ፣ ሞዛምቢክና ማላዊ) ልምድ ያመላክታል።

በግብርና ምርት ውል የተሰማራ አምራች በቡድን በመደራጀትም ሆነ በተናጠል፣ በኩታ ገጠም እርሻ የተለያዩ በገበያ ተፈላጊ የሆኑ የግብርና ምርቶች በጥራት፣ በተፈለገው መጠንና ጊዜ በማምረት ለግል ባለሃብቶች፣ ለካምፓኒዎች፣ ለመንግስታዊ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅቶች፣ ፋብሪካዎች በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ተገቢና ወቅታዊ የሆነ የገበያ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ስምምነት በማድረግ የምርት ግብይት ያከናውናሉ ማለት ነው።

## 7.2. የግብርና ምርት ውል ጠቀሜታና ውስንነት

### 7.2.1. የግብርና ምርት ውል ጠቀሜታ

በግብርና ምርት ውል አሰራር በአነስተኛ ደረጃ ለሚገኙ አርሶ/አርብቶ አደሮች፣ ወጣቶችና ሴቶች፣ ኩባንያዎች፣ ኢንተርፕራይዞች፣ ፋብሪካዎችና ሌሎች

በትስስሩ ለታቀፉ አካላት የሚያስገኘው ጠቀሜታ በርካታ ሲሆን ዋና ዋናዎቹም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

**ሀ/ ለአምራቹ የሚሰጠው ጠቀሜታ**

በግብርና ምርት ውል የአመራረትና የገበያ ስርአት የሚታቀፉ አርሶ/ከፊል/ አርብቶ አደሮች (ወጣቶችና ሴቶች/እማወራዎች) ከምርት ተረካቢ/አስመራች ባለሀብቶችና ኩባንያዎች ጋር በሚፈጥሩት ትስስር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በርካታ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን የሚያገኙ ሲሆን በዋናነት፡-

- ✓ አስቀድሞ የታወቀና የተረጋገጠ ገበያ ይኖራቸዋል፤በውጤቱም የገበያው ተጠቃሚ ይሆናሉ፣
- ✓ የግብይት ሰንሰለትን ያሳጥራል፣
- ✓ በዋጋ መዋዠቅ ምክንያት ሊደርስ ከሚችለው ስጋት ይድናሉ
- ✓ የግብርና ግብአት ብድር አቅርቦትና የቴክኒክ ድጋፍ (የኤክስቴንሽን፣ የስልጠና፣ የምክር ወዘተ) ድጋፎች ይመቻቻሉ፣
- ✓ ከአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ጋር እንዲተዋወቁ አመች ሁኔታ ይፈጠራል፣
- ✓ የመሬት አጠቃቀማቸው ይሻሻላል፣
- ✓ ምርታማነትና የምርት ጥራት ይጨምራል፣
- ✓ የግብዓት አቅርቦት (ምርጥ ዘር/ችግኝ፣ ማዳበሪያ፣ የኬሚካል፣ ጥራቱን የጠበቀ ምርት ማሰባሰቢያ ቁሳቁሶች ወዘተ) ይመቻችላቸዋል፣
- ✓ የምርት ማጓጓዣ ትራንስፖርት፣ ምርት መሰብሰቢያ ቁሳቁሶች ወዘተ ተደራሽ ይሆናል።
- ✓ የእውቀትና የክህሎት ሽግግር ያመጣል

- ✓ በእነዚህና ሌሎች ድጋፎች የአምራቹን አሰራር በማዘመን ምርትና ምርታማነትን ይጨምራል፤ በሒደትም ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቱ ይረጋገጣል።

**ለ/ ለአስመራቹ ያለው ጠቀሜታ**

- ✓ አምራቾች ጋር በመስራቱ የመሬት ችግርን ያቃልለታል፤
- ✓ የማምረቻ ወጪዎችን ይቀንስለታል
- ✓ አስተማማኝ፣ ጥራቱን የጠበቀ እና ቀጣይነት ያለው የምርት አቅርቦት ያገኛል፣
- ✓ ከውስጥና በውጭ ከሚገኙ የንግድ ሸሪኮቹ ጋር ጠንካራና ቀጣይነት ያለው የገበያ ትስስር እንዲፈጥር፣ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆን ይረዳዋል፤
- ✓ አምራቹ በአስመራቹ አሰራር ላይ የእኔነት ስሜት እንዲሰማው ያደርጋል በዚህም የአስመራቹ ቀጣይነት ይረጋገጣል።
- ✓ ሰላማዊና ዘለቄታ ያለው ኢንቨስትመንት እንዲካሄድ ያግዛል ይጫወታል/ win — win/Sustainable Investment

**ሐ/ ለአካባቢው ማህበረሰብ**

- ✓ የስራ እድል ይፈጥራል።
- ✓ የመሰረተ-ልማት ድጋፎች (ለምሳሌ፡- የጤና፣ የት/ቤት፣ መንገድ፣ መብራት ወዘተ) ግንባታ፣
- የአቅም ውስኑነት ያላቸውን ተማሪዎች ከፍተኛ የትምህርት
- ተቋማት ማለትም እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ ልከው ያስተማሩ
- ድርጅቶች እንዳሉ በጥናታችን ለመረዳት ተሞክሯል።
- ✓ በክልል/በዞን/በወረዳ በሚኖራቸው የተለያዩ የልማት እንቅስቃሴዎች

ላይ በተለያየ መንገድ ድጋፍ በማድረግ (ገንዘብ መዋጮ፣ የመኪና ድጋፍ ወዘተ) ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ነው፡፡

**መ/ ለመንግስት/ለሀገር**

- ✓ መንግስት ከግብአት አቅርቦት/ከኤክስቴንሽን ድጋፍ አንጻር ያለበትን ከፍተኛ ጫና ይቀንስለታል፡፡
- ✓ ከውጭ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በማስቀረት የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ይቀንሳል፡፡
- ✓ የኤክስፖርት ምርት አቅርቦት በማሳደግ፣የውጪ ምንዛሪ ያስገኛል፡፡

**7.2.2. የግብርና ምርት ውል ውስንነቶች**

**ሀ. ከአምራቹ አንፃር**

- ✓ ከሚጠቀመው አዳዲስ ቴክኖሎጂ ጋር ቶሎ ያለመላመድ
- ✓ የምርት ገበያ ዋጋ መዋዠቅ (Market failures) (የዋጋ ማስተካከያ በውሉ ላይ ካልተካተተ)
- ✓ ከአስመራቹ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የመደራደር አቅም አለመኖር
- ✓ በተለያዩ ምክንያቶች የግብዓት አቅርቦትና የምርት ግብይት ክፍያ መዘግየት (ለሌላ ገዢ መሸጥ)
- ✓ አምራቹ አንድ አይነት ሰብል ብቻ ቢያመርቱ ወይም ለአካባቢው ያልተለመደ የሰብል ዝርያ ቢሰጣቸው ይህ ባልተጠበቀ ሁኔታ
- አካባቢን ሊጎዳ ይችላል ለምሳሌ በበሽታዎች መልክ፡፡
- ✓ አስመራች ግልፅ የሆነ የዋጋ አተማመን፣ የምርት መጠን እና የጥራት መለኪያ ዘዴ ወይም ለአምራቹ በቀላሉ በማይረዳው መልኩ መመዘኛ ማስቀመጥ (ለምሣሌ የላቦራቶሪ ውጤት በማሳየት)

### ለ. ከአስመራች አንፃር

- ✓ የህግ ማዕቀፉ ተግባራዊ ባለመደረጉ ምክንያት አምራቹ ውል በማፍረስ ለሌላ ገዢ ምርቱን የመሸጥና አስመራቹን ለአላስፈላጊ ወጪ ማጋለጥ፡ ፡
- ✓ አምራቹ የቀረበለትን የምርት ማሳደጊያ ግብዓት በአግባቡ ባለመጠቀም በምርትና ምርታማነት ላይ ተፅእኖ ከማሳደሩም በላይ በአስመራቹ ላይ አምነት ማጣትና የአቅርቦት ችግር እንዲያጋጥመው ያደርጋል፡፡
- ✓ የማህበረሰቡ ባህልና ማህበራዊ እሴቶች በተጨማሪም በህግ አስመራቹ የሚፈልገውን ምርት ዓይነት በሚፈልገው መሬት ላይ እንዳያመርት የሚከለክል ሊሆን ይችላል፤

## 7.3. በአምራችና አስመራች መካከል ሊኖሩ የሚችሉ የግብርና ምርት ውል ዓይነቶች (ሞዴሎች)

### 7.3.1. የተቀናጀ ውል ሞዴል (Nucleus State Model)

“የተቀናጀ ውል” ማለት የግብርና ምርት ውል ዓይነት ሆኖ አስመራች የራሱ ይዞታ ኖሮት በማምረት ተግባር የተሰማራ ነገር ግን የሚፈልገው የምርት መጠን በቂ ባለመሆኑ በዙሪያው ካሉ አነስተኛ ይዞታ ካላቸው አርሶ/አርብቶ አደሮች እና ከሌሎች ፈቃድ ካላቸውና በግብርና ምርት ማምረት ከተሰማሩ ባለሃብቶች ጋር የሚያደርገው የግብርና ምርት ውል ስምምነት ነው፤

- ✓ አስመራቹ የራሱ የሆነ እርሻ ኖሮት ለተጨማሪ ምርት በዙሪያው በግብርና ምርት ውል መሰረት ያስመርታል፡፡
- ✓ የግብርና ማቀነባበሪያው ከእርሻ ማሳው በቅርብ እርቀት ሊገኝ

ይችላል።

- ✓ ይህ ሞዴል አስመራቹ የፋብሪካውን ምርት በተወሰነ መጠን እንዲሸፍን ታሳቢ ያደረገ ነው።
- ✓ ከተሰማራበት የግብርና ምርት ጋር ተያያዥነት ያላቸው በቋሚ ሰብሎች ሲሆን፣አትክልት ልማት፣ፍራፍሬ ልማትና የሸንኮራ አገዳ ምርትን እንዲሁም የእንስሳት እና የእንስሳት ተዋፆ ምርቶችን ያጠቃልላል።
- ✓ አስመራቹ በራሱ ማሳ ላይ የሰርቶ ማሳያ በማዘጋጀት ለአምራቹ በማሳየት የምርቱን ተቀባይነት ለማረጋገጥ ሊሰራ ይችላል፤
- ✓ አስመራቹ የምርት ጥራቱን ለማሰጠበቅ ተከታታይና ቀጣይነት ያለው የሙያዊ ድጋፍና ክትትል ሥርዓት ይጠቀማል።

ይህ ሞዴል በግብርና ውጤቶች ማቀነባበር የተሰማሩ ባለሃብቶች መሬት ወስደው የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ ምርት በራሳቸው ማሳ ዙሪያ ያሉ አርሶአደሮች በማደራጀት በግብርና ምርት ውል መሰረት የማስመረት ሥራ የሚሠሩበት ሞዴል ሲሆን አስመራቹ ለአምራች አርሶ አደሮች የሚከተሉትን ሊያሟላ ይችላል(ማሟላት ይጠበቅበታል) እነዚህም፦

- ✓ ብድር የማመቻቸት
- ✓ ግብዓት የማቅረብ
- ✓ የስልጠናና የሙያ ድጋፍ የመስጠት
- ✓ የትራንስፖርት አገልግሎትና ሌሎች ድጋፎች በመስጠት ምርትና ምርታማነቱን ለማሻሻል የሚያስችል ስራ መስራት ይጠበቅበታል።

### 7.3.2. የተማከለ ውል" (Centeralized model)

የተማከለ ውል ማለት የግብርና ምርት ውል ዓይነት ሆኖ አስመራች የራሱ የሆነ የማምረቻ ይዞታ ሳይኖረው በቀጥታ/በራሱ በማምረት ተግባር ውስጥ ሳይገባ ከአምራቹ ጋር የሚያደርገው የግብርና ምርት ውል ስምምነት ነው፤ ይህ የግብርና ምርት ውል ሞዴል ብዙ ጊዜ ተግባራዊ የሚደረገው በኢንዱስትሪ ሰብሎች ላይ ሲሆን ሌሎችም ላይ ማለትም ለዶሮ ምርት (ዕንቁላልና ሥጋ)፣ ወተት፣ትኩስ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

አስመራቹ ጥራቱን የጠበቀና የተሻለ ምርት እንዲመረትና የራሱንና የገበሬዉን ተጠቃሚነት ከፍ ለማድረግ ለአምራቹ ገበሬ የተቀናጀ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፡ ፡ ከድጋፎቹም መካከል ፡-

- ብድር ማመቻቸት፣
- ግብዓት ማቅረብ፣
- ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣
- የመሰኖ መሰረተ ልማትና ማቀነበበሪያ ፋብሪካዎችን መገንባት፣
- የትራንስፖርት አገልግሎት ድጋፍ በመስጠት ምርትና ምርታማነቱን ለማሻሻል የሚያስችል ስራ መስራት ይጠበቅበታል፡፡

ይህ ሞዴል በተለይ አምራች ኢንዱስትሪዎች በኢንዱስትሪ ወይም ኤክስፖርት ሰብል ልማት ከተሰማሩ ባለሃብቶች ጋር ውል በመውሰድ ሊተገበር ይችላል፡፡

### 7.3.3. በርካታ ተዋናኞች የሚሳተፉበት የውል ግብርና ሞዴል (Multipartite)

“የባለብዙ ተዋንያን ውል” ማለት የግብርና ምርት ውል ዓይነት ሆኖ አስመራች

እና አምራች በበጎ ፈቃዳቸው በሶስተኛ ወገን ድጋፍ እና ማስተባበር የሚከናወን የግብርና ምርት ውል ስምምነት ነው።

- ➢ የውል አስተዳደሩ ብዙ ጊዜ የመንግሥት አካላት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ድርጅቶችን ያካተተ ነው።
- ➢ የግብዓትና ብድር አቅርቦትና ሙያ እገዛ የሚሰጡ መንግሥታዊ ያልሆኑ፣ፋይናንስና ግብዓት አቅራቢ ተቋማት ሊካተቱ ይችላሉ።
- ➢ በቀላሉ ሊተገበር የሚችል የግብርና ምርት ውል ሞዴል ነው።

### 7.3.4. አገናኝ ሞዴል (Intermediary model)

- የአገናኝ ውል" ማለት የግብርና ምርት ውል ዓይነት ሆኖ በአምራቹ ፈቃድ ማንኛውም ሰው አምራቹን ወክሎ ከአስመራቹ ጋር የሚያደርገው የግብርና ምርት ውል ስምምነት ነው።
- ➢ በአምራቹ ፈቃድ (ማህበር ወይም ዩኒየን ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ) አምራቹን ወክሎ ከአስመራቹ ጋር የሚያደርገው ስምምነት ነው።
- ➢ አስመራቹ ለአምራቹ በአገናኙ በኩል የኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ ብድርና ግብዓት ያቀርባል። እንዲሁም አገናኙ ለአስመራቹ ምርቱን ከአምራቹ በመቀበል የሚያቀርብ ይሆናል፤ ምርት ግዥ በመፈጸም ለአስመራች ያቀርባል።

### 7.3.5. መደበኛ ያልሆነ ውል (Informal Model)

በማህበረሰቡ ባህልና እሴት መሰረት በአምራችና አስመራች መካከል የቃል መግባባት ላይ መሰረት ያደረገ በፅሁፍ ያልተደገፈ የግብርና ምርት ውል

ዓይነት ነው።

- ✓ ጊዜያዊና ግምታዊ ሁኔታዎች የሚንጸባረቅበት ሆኖ ከፍተኛ ወጪ የማይጠይቁ ምርቶች ላይ ትኩረት ያደርጋል።
- ✓ የረጅም ጊዜ ታማኝ ግንኙነትን መሰረት አድርጎ ሊፈጸም የሚችል የግብርና ምርት ውል ዓይነት ነው።
- ✓ በቃል የሚደረግ ስምምነት በመሆኑ በህግ ለመዳኘት ስለሚያስቸግር በአዋጅ ቁጥር 1289/2015 ከማይተገበሩት የግብርና ምርት ውል ሞዴል አንዱ ነው።

## 8. ግብርና ምርት ውል ቅድመ ዝግጅቶች

እንደሚታወቀው የግብርና ምርት የውል ስምምነት አሰራር ተነሻስነቱን ወስዶ የሚጀምረው ከአስመራቹ ወይም  ከሶስተኛ ወገን ቢሆንም የውል ስምምነቱ በሁለቱም ወገኞች ማለትም በአምራችና በአስመራች የውልሀሳብ መሰረት በቃልም ሆነ በፅሁፍ ሊያቀርብ ይችላል። ለውጤታማ የግብርና ምርት ውል አተገባበር  ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ ይረዳል። ለአተገባበሩ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ-ዝግጅቶች የሚከተሉት ናቸው።

### 8.1. ትስስሩ የሚካሄድበት አካባቢ ማወቅና መለየት

አስመራች ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የሚሰራበትን አካባቢ ማወቅና በአካባቢው ሕብረተሰብ የተለመዱትን ነባርና ልማዳዊ አሰራሮች በመለየት የተሻሻሉ አሰራሮችንና ተገቢውን ምክረ-ሃሳብ ተከትለው እንዲሰሩ የሚያስችል የንድፈ-ሃሳብና የክህሎት አቅም ግንባታ ስራዎችን በስፋት ማካሄድ ይገባዋል።አስመራቹ የሚከተሉትን የቅከድመ-ዝግጅት ሥራዎችን ሊተገብር ይገባል።

- ✓ የማሕበረሰቡን ባህላዊ እሴቶች አመለካከትና ልምዱን ማወቅና መገንዘብ፣
- ✓ የሚመረተው ምርት ለአካባቢው ስነ-ምህዳር ተስማሚ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ✓ በቂ የሆኑ መሰረተ ልማቶች /መንገድ፣ ቴሌ፣ መብራት፣ መስኖ መኖራቸውን ማረጋገጥ ፣
- ✓ በቂ የሆነ የማምረቻ መሬት መኖሩን ማረጋገጥ፣
- ✓ የምርት ማሳደጊያ እና ጥራት ማሻሻያ ግብዓት የሚገኝበትን ምንጭ ማረጋገጥ፣
- ✓ በአካባቢው በቂ የሰው ኃይል መኖሩን ማረጋገጥ፣

### 8.2. የግብርና ምርት ዓይነትን እና መጠንን አስቀድሞ መወሰን

የግብርና ምርት ውል አሰራር ቅድሚያ የሚሰጣቸው እና ትስስር የሚፈጠርባቸውን አትራፊ የግብርና ምርቶች በመለየት ይጀምራል፡፡ አስመራቹ ለዓለም አቀፍና ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚቀርቡ፣ለፋብሪካ ጥሬ እቃ የሚውሉ የተመረጡ የግብርና ምርት አይነቶችን በማስመረት ተወዳዳሪና ትርፋማ የሚሆን ሲሆን አምራቹም የቀረበለትን አዳዲስ የግብርና ምርት ዓይነት እንዲሁም ቴክኖሎጂ በማላመድና በመጠቀም፣የቴክኖሎጂና እውቀት ሽግግርን በመተግበር፣ዘላቂና መሰረታዊ የአመራረት ስልት በመከተል ተጠቃሚነቱን ማረጋገጥ ይችላል፡፡አምራቹም አስመራቹም በመረጡት የግብርና ምርት ዓይነት እና መጠን ተመሳሳይ ፍላጎት በማሳየት ለጋራ ተጠቃሚነት በሚረዳ መልኩ ስምምነቱን ማድረግ ይችላሉ፡፡

### 8.3. በሀገሪቱ የግብርና ምርት ውልን የሚያበረታታ የህግ ማዕቀፍ መኖሩን እና ተፈፃሚነት ማረጋገጥ

የግብርና ምርት ውል ስምምነት ከህግ ጋር በእጅጉ የተያያዘ እንደመሆኑ መጠን የፖሊሲ መኖር በአምራችና በአስመራች መካከል ለሚፈጠረው የግብይት ስምምነት አፈፃፀም የህግ ሽፋን እንዲኖረውና በሁለቱም ወገኖች ፍትሀዊ የሆነ ተጠቃሚነት እንዲሰፍን አዎንታዊ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ስለሆነም ሁለቱም ወገኖች በእኩል አይን የሚመለከት የህግ ማዕቀፍ መኖሩ ማረጋገጥና የህግ ማዕቀፉን ይዘት በውል መቃኘት ያስፈልጋል፡፡ በፌደራልና በክልል ያለውን የህግ ማዕቀፍ አፈፃጸም ደረጃቸውን መገምገም በእጅጉ ያስፈልጋል፡፡

## 9. የግብርና ምርት ውል አሰራር ስርዓት አደረጃጀት

(አርሶ/ከፊልአርብቶአደሮች/ ሴቶችና ወጣቶች ቡድን አደረጃጀት)

የግብርና ምርት ውል በአነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደሮች በአነስተኛ ማሳ ላይ ለመተግበር የሚያግድ ምንም ዓይነት ሁኔታ የተቀመጠ የለም፡፡ ሆኖም ግን አምራቹ በግል ምርቱን ገበያ ከማቅረብ ይልቅ በቡድን ወይም በክላስተር ቢያመርቱ ወይም ቢያቀርቡ የገበያው ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ የቡድን ግብይት ማድረግ በገበያው የሚሳተፉትን ኃይል ያበረታታል፣ የመወሰን ሀይላቸውን ያጠናክራል፣ ከብዝበዛም ያድናል፡፡ አምራቾች በፈጠሩት በአደረጃጀታቸው በኩል በሚፈፅሙት ግብይት ባለሃብቱ/ፋብሪካው/ ካምፓኒው ለአገልግሎት የሚያወጣውን ወጪ የሚቀንስለት ሲሆን አምራቹ ምርቱን ለባለሃብቱ /ለፋብሪካው/ ለካምፓኒው በሚያቀርብበት ጊዜ የማጓጓዣ ወጪ ይቀንስልታል፡፡

አስመራቹ የሚፈልገውን የምርት መጠንና ጥራት ለማስጠበቅ ሲባል የሚሰጠውን የሙያ ድጋፍና ክትትል ስርዓቱን ቀልጣፋ ከማድረጉም በላይ አምራቾች ምርታቸውን ለገበያው በሚያቀርቡበት ጊዜ ከካምፓኒው ጋር በሚፈጥሩት የውል ስምምነት አመኔታን ከማሳደሩም በተጨማሪ ብዙሀን አርሶ አደሮች እርስ በርስ በመወያየት የቴክኖሎጂ ሽግግር እና አጠቃቀምን በቀላሉ ሊረዱ ይችላሉ፤ ለችግራቸውም የጋራ የሆነ የመፍትሄ ሀሳብ ያገኛሉ፤ እንዲሁም የተለያዩ መልዕክቶችን በቀላሉ ማስተላለፍ ይቻላል። ስለዚህም በቡድን መደራጀት የገበያውን ቀጣይነት ከማረጋጡም ባሻገር እንደ መማማሪያ መድረክ ሊታይ ይገባዋል። በመሆኑም  አምራቾች በቡድን ተደራጅተው ምርታቸውን በግብርና ምርት ውል ማቅረብ ቢችሉ ሁሉም የግብርና ምርት ውል ተወናዋዮች የተሻለ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

በትስስሩ የሚሳተፉ አምራቾች  ከሚመለከታቸው የክልል እና የፌደራል የመንግስት ተቋማት  በዋናነት በየደረጃው ያሉ ህብረት ስራ ኮሚሽን እና ግብርና መ/ቤቶች ጋር በመቀናጀት አምራቾች  ከማደራጀት አንጻር ሀገሪቷ ያወጣቻቸውን ህግና ደንብ በጠበቀ መልኩ እንዲደራጁ ይደረጋል። ይህም አምራቹ የሚተዳደርበት ደንብ ይኖረዋል ማለት ነው።  በመሆኑም በማህበሩ የተመረጡ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች እና እያንዳንዱ አባላት  ድርሻቸው እና ኃላፊነታቸው በግልጽ ስለሚታወቅ የስራዎችን በቁርጠኝነትና በኃላፊነት የመወጣት አካሄዶች ይፈጠራሉ።

በግብርና ምርት ውል ትስስር የሚፈጥሩ አምራቾች በቡድን ለመደራጀት ተመሳሳይ ፍላጎት ኖሯቸው በኢትዮጵያ የአደረጃጀትና የውክልና አሰጣጥ ህግና

ደንብ መሰረት ያደረገ ሆኖ የራሳቸውን መሪዎች ስመምረጥ የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ይሆናል፤ እነዚህም፤-

- ✓ በአንድ መንደር የተሰባሰቡና የጋራ ፍላጎት ያላቸው ሆኖ በአንድ ቡድን የሚደራጁ አባላት ቁጥራቸው እንደ አካባቢው አመቺነት የሚወሰን ይሆናል።
- ✓ እያንዳንዱ ቡድን የሚወክለውን መሪ በመምረጥ የተመረጠው አካል በተሰጠው ውክልና መሰረት ከአምራቹ ጋር የሚገናኝ ይሆናል፤

የቡድኑ ተወካዮች ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እንደአስፈላጊነቱ በቡድን አባላት በሙሉ ወይም በአብላጫ ድምጽ የሚመረጡ ይሆናሉ።

## 10. የውል ስምምነት ሰነድ አዘገጃጀትና አጠቃቀም

የህጉ ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ በአምራቹና አስመራች መካከል በሚደረገው የግብርና ምርት ውል ስምምነት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች ማካተት ይኖርበታል። እያንዳንዱ የውል ይዘት የራሱ የሆነ ልዩ ባህርይ ሊኖረዉ ስለሚችል ቢያንስ የሚከተሉትን መሰረታዊ መስፈርቶችን ያካተተ ሊሆን ይችላል፡-

1. **የገበያ መስፈርት፡-** በዚህ መስፈርት የምርት ዓይነት፣ የምርት መጠን፣ የጥራት ደረጃ፣የማጓጓዣና የገበያ ቦታ ወጪዎች፣ የምርት ዋጋ እና የግብዓት አቅርቦት መወሰን ይኖርበታል።
2. **የሃብት መስፈርት፡-** አስመራቹ ለግብርና ምርት ውል የሚበቃ አስፈላጊው የገንዘብና የቁሳቁስ ባለቤት መሆኑ፣የገቢ ዋስትና እንዲሁም የግብዓት አቅርቦት መኖሩን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሲሆን በአምራች ደረጃም ለግብርና

ምርት ውል ክዋኖ የሚሆን በቂ የእርሻ መሬት፣የእንስሳት ኃብት ወ.ዘ.ተ.ሊያሟላ ይገባል፡፡

3. **የሥራ አመራር መስፈርት:-** ይህ መስፈርት እንደየ ሁኔታው በቅድሚያ የዋጋ ተመን አሰራርን፤ የግብርና ግብዓት አቅርቦትን፤ የቴክኒክ ድጋፍ እና አስተዳደራዊ ቁጥጥርን የሚያካትት ነው፡፡

4. **የመሬት ባለቤትነትና ባለይዞታነት መስፈርት:-** በዚህ መስፈርት ውስጥ አምራቹ በባለቤትነት በመሬቱ ሊያመርትበት መቻሉን የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ መኖሩ የሚፈተሽበት ነው፡፡

በመሆኑም ዝርዝር የውሉ ይዘት ቢያንስ የሚከተሉትን ያቀፈ መሆን ይገባዋል፡-

1. የአምራቹ እና የአስመራቹ ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣ቀን እና ፊርማ፣
2. የኢንቨስትመንትና የንግድ ፈቃድ ቁጥር
3. የግብርና ምርት ውሉ ዓላማና ግብ፣
4. የማሳው ወይም የማራቢያ ቦታ ስፋትና አዋሳኞች ወይም የሚራባዉ ዓይነትና ብዛት
5. የአምራቹ እና የአስመራቹ መብትና ግዴታዎች በዝርዝር ማስቀመጥ፣
6. የምርት አይነት፤ ጥራትና የመጠን መግለጫ መስፈርቶች፣
7. የግብዓት እና የምርት ዋጋ አወሳሰን እንዲሁም የአከፋፈል ሁኔታ፤
8. የማጓጓዣ ሥርዓትና የወጪ አሸፋፈን
9. የቴክኒክ ድጋፍ ዓይነቶች፤
10. እንደ አግባብነቱ የአዳቃዮች እና የአዕምሮ መብት ባለቤትነትን የተመለከቱ ድንጋጌዎች፣

11. ውሉ እንዳይፈጸም ማድረግ የሚችሉ ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች
12. የተዋዋይ ወገኖች ወራሽ ወይም ተተኪ መብትንና ግዴታን ስለማስተላለፍ የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፣
13. የግብርና ምርት ውሉ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ፤ ስለሚሻሻልበት ወይም ስለሚቀየርበት፤ ስለሚቋረጥበት ሁኔታዎችና ሥነ-ስርዓት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፣
14. አለመግባባቶችን መፍቻ መንገዶች፤
15. በምርት ውሉ መሰረት የምርቱ ጥራትና መጠን በመቀነስ ወይም በመጨመር ልዩነት ቢፈጠር የዋጋ ሥሌት ማስተካከያ ስለሚደረግበት፣
16. የምርት ርክክብ የሚደረግበት ቦታና ጊዜ እንዲሁም የማጓጓዣ ስርዓት
17. የግብርና ምርት ውሉ የተፈጸመበት ጊዜና ቦታ
18. የግብርና ምርት ውል ስምምነት በሚፈፀምበት ጊዜ የነበሩ እማኞች ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣ቀን እና ፊርማ
19. የውል ስምምነት ሰነዱ አግባብ ባለው አካል መመዝገብ

አንዳንድ ህጋዊ ሰነዶችና የአፈፃፀም መመሪያና ደንቦች እንደአስፈላጊነቱ ከዋናው የውል ሰነድ ጋር በአባሪነት ተያይዘው ሊገኙ ይገባል።

## 11. የምልመላ መስፈርት

በግብርና ምርት ውል ትስስር ውስጥ በዋናነት ተዋናይ ሆነው የሚሰሩት አካላት አስመራቹ (ባለሀብቱ/ኩባንያው/ፋብሪካው/ኢንተርፕራይዙ) እና አምራቹ (አርሶ/አርብቶ አደሩ፣ ከፊል አርሶና አርብቶ አደር፣ ማህበራት/ዩኒየኖች እንዲሁም በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች ሲሆኑ በስርአቱ ለመታቀፍ ተዋናያዎቹ ማሟላት

የሚገቧቸው መስፈርቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፤

ትስስሩ ውጤታማ ሆኖ ሁለቱም ተዋናዮች ላይ ዘለቄታዊ ለውጥ ለማምጣት ይቻል ዘንድ የምልመላ መስፈርት በይበልጥ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ሲሆን በአስመራቹም ሆነ በአምራቹ በኩል መታየት የሚገባቸው መሰረታዊ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

### ፲.፩. የአስመራች መመልመያ መስፈርት

- ✓ የግብርና ምርት ለማስመረት ፍላጎት ያለው
- ✓ በዘርፉ የታደሰ ንግድ ፍቃድ
- ✓ የግብርና ኢንቨስትመንት ፈቃድ ያለው(ለተቀናጀ ውል)
- ✓ በግብርና ምርት ውል የሚሳተፉበት የሀብት መጠን የሚገልጽ የአጭር ጊዜ የባንክ ስቴትመንት (የ6 ወራት) እና በውጪ ኦዲት የተደረገ የሂሳብ ሪፖርት
- ✓ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያለው
- ✓ ቢዝነስ ፕላን አዘጋጅቶ ማቅረብ የሚችል
- ✓ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች የመስጠት አቅምና ፍላጎት ያለው
- ✓ ግብአት የማቅረብ አቅምና ፍላጎት ያለው፤
- ✓ በግብርና ምርት ውል ትስስር ለሚሳተፉ አምራቾች ወቅታዊ ስልጠናዎችን በመስጠት የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን የሚችል፤
- ✓ በገባው ውል መሰረት ክፍያ መክፈል የሚችል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

### 11.2. የአምራች መመልመያ መስፈርት

- ✓ በውል ግብርና ትስስር ለመሳተፍ ፈቃደኛና ታማኝ የሆነ/የሆኑ፣
- ✓ ህጋዊ የሆነ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያላቸው ወይም ህጋዊ የሆነ ቢያንስ የአንድ ዓመት የመሬት ኪራይ ውል ያለው ለአመታዊ ሰብሎች፤ ለቋሚ ሰብሎች ቢያንስ አስር አመት የመሬት ኪራይ ውል ያለው፤
- ✓ የግብርና ልማት ስራ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው፣
- ✓ ለመማር ወይም ትክክለኛውን ምክረ-ሃሳብ ተከትለው ለመስራት ፈቃደኝ የሆኑ፤
- ✓ ምርታቸውን በገቡት ውል መሰረት በጥራት ለማቅረብ ፈቃደኛ የሆኑ
- ✓ ህብረት ሥራ/ዩኒያን ከሆነ የምዝገባ ምስክር ወረቀት እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ የምርትና የግብአት መጋዘን ያለው፤
- ✓ ለምርት ጥራትና መጠን የሚያስፈልጉ /በአስመራች የሚቀርቡ/ ግብዓቶችና የቴክኖጂ ውጤቶችን በአግባቡ ለመጠቀም ፍቀደኛ የሆነ

## 12. የፈጻሚዎችና ባለድርሻ አካላት የስራ ድርሻ

በግብርና ምርት ውል አፈፃጸምና አተገባበር ላይ የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የአርሶ አደሮች ማሕበራት ዕምነትና ተሳትፎ ካልታከለበት የአርሶ አደሩን አመኔታ አግኝቶ ሥራውን በተግባር ለማዋል አስቸጋሪ ያደርገዋል፡ ፡ ስለዚህም ለውሉ ስምምነት መሳካት ግብርና ሚ/ር ከክልል ግብርናና ሌሎች የሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት /ድርጅቶች/ ጋር በመሆን በአስመራችና በአምራች መካከል ጠንካራ ትስስርና እምነት እንዲፈጠር

አስፈላጊውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ከላይ የተገለፁትን አካላት በግብርና ምርት ውል ውስጥ እንደ እማኝ አድርጎ በማካተት የአርሶ አደሩን እምነት ከፍ ማድረግና ማጎልበት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለግብርና ምርት ውል አተገባበር ድርሻ አላቸው ተብለው ሚገመቱ ተቋማት የስራ ድራሻና ኃላፊነት እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### 12.1. የግብርና ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

የግብርና ምርት ውል ትስስር ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን በሚኒስቴሩና በክልል ግብርና ቢሮዎች በኩል የሚከተሉት ተግባራት በቅንጅት ይከናወናሉ፡፡

- ✓ በተዋንያን (በአምራችና በአስመራች) መካከል የሚፈፀመው ውል በግብርና ምርት ውል አዋጅ ቁጥር 1289/2015 መመሪያና ደንብ መሰረት መሆኑን ማረጋገጥና መከታተል፡፡
- ✓ በየደረጃው ላሉ የግብርና ውል ተዋናዮች ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣ ክትትልና ግምገማ ማድረግና ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር ማጠናቀርና ማስፋት እንዲሁም ስራዎችን ለመከወን ስርዓት መዘርጋት፡፡
- ✓ በሀገሪቱ ያለውን የግብርና ምርት እምቅ ሀብትና እድሎችን በዲጂታልይዜሽን የመረጃ ስርዓት በመያዝ ተደራሽ ማድረግ፡፡
- ✓ ከሁለት ክልሎች በላይ ተሳተፊ ለሆኑ የግብርና ምርት አስመራቾችና አምራቾች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መስጠት፡፡
- ✓ የግብርና ምርት ውል ትስስር በማስፋት ሌሎችንም አስመራችና አምራቾችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማነሳሳትና በመደገፍ ቀጣይነቱን ማረጋገጥ፤

- ✓ የመሰረተ ልማት አውታሮች ማሟላት
- ✓ በሌሎች ችግር መፍቻ ዘዴዎች መፍታት የማይቻሉትን አለመግባባቶች ቢፈጠሩ በሕግ አግባብ እንዲፈቱ ማመቻቸት
- ✓ ያለመግባባቶችን ምንጭና ሁኔታ በማጥናትና በማደራጀት ለሚመለከተው አካላት ችግር ፈቺ የምክረ ሃሳብ ማቅረብ
- ✓ በግብርና ምርት ውል ተዋንያን የአካባቢ ጥበቃ ላይ ትኩረት እንዲሰጡ መከታተል እና መደገፍ ፤
- ✓ የግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች ለግብርና ምርት ውል ተዋንያን ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ
- ✓ የምርምር ተቋማት ለግብርና ምርት ውል አካባቢዎች የሚሆኑ የተሻሻሉ አዳዲስ ዝርያዎችንና ቴክኖሎጂዎችን በማውጣት በኩል ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ፤
- ✓ የኢንሹራንስ የዋስትና መብት ያላቸውን አምራቾችና አስመራቾች በሚገጠማቸው የአደጋ ጊዜ የማካካሻ ዋስትናቸው የተረጋገጠ መሆኑን መከታተል።
- ✓ የተፈጥሮ አደጋዎች እንደ ጎርፍ የመሬት መንሸራተት የተባይ ክስተት የመሳሰሉትን አደጋዎች ይመዘግባል፤ መረጃ ያደራጃል፤ ሪፖርት ያደርጋል።
- ✓ የአምራቾችን የግብርና ምርት የማምረትና ጥራት ላይ ክህሎትና አቅምን ለማሳደግ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን፣ መደገፍ፤
- ✓ በቡድን አደረጃጀት ሂደት ድጋፍ መስጠት፤

- ✓ በውል ግብርና ለተሰማሩ አምራች ህብረት ስራ ማህበራት፣ ባለሀብቶች እና አርሶአደሮች ግብዓት፣ብድር እና ልዩ ልዩ ቴክኖሎጅዎች እንዲቀርቡላቸው ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።
- ✓ በግብርና ምርት ውል የሚመረት ምርት መረጃ ማጠናቀር ጠቅላላ የአሰራር ስርዓቱን መከታተል እና ለሚለከተው አካል ሪፖርት ማቅረብ፤

### 12.2. የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተግባርና ኃሊፊነት

- ✓ በግብርና ምርት ውል ምርቶች የገበያ መረጃ ያጠናቅራል፤ ይከታተላል፣ተደራሽ ያደርጋል፤
- ✓ በግብርና ምርት ውል ተዋንያን በገቡት ውል መሰረት ግብይት እንዲፈጸም ይከታተላል፤
- ✓ የኤክስፖርት ምርት የውል ምዝገባ አገልግሎት ይሰጣል ያከናውናል፣አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤
- ✓ በግብርና ምርት ውል አፈጻጸምን በተመለከተ በመስክ ግምገማዎች ላይ በቅንጅት ይሰራል፣
- ✓ አምራቾችና አስመራቾች ያመረቱትን ምርት ወደ ውጪ እንዲላኩ መስኪያ ፈቃድ እና የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል፤

### 12.3. የህብረት ስራ ኮሚሽን ሚና

- ✓ ከግል ይልቅ በማህበር ወደ የግብርና ምርት ውል መግባት የሚፈልጉ አርሶ አደሮችን በማህበር ማደራጀት
- ✓ በማህበር/በዩኒየን ተደራጅው በውል ግብርና የተሰማሩ አምራች/

አስመራች ያለባቸውን ክፍተት በመለየት ማህበሩን የማጠናከር ስራ ይሰራል፤

### 12.4. መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሚና

- ✓ የአምራቾችን የአመራረት፣የጥራት አያያዝና የፋይናንስ ክፍተት በመለየት አቅማቸውን ማጠናከር፤
- ✓ የግብርና ምርት ውል ለማስፋትና መሰረት ለመጣል የማስተዋወቅና ግንዛቤ የመፍጠር ስራ መስራት
- ✓ በግብርና ምርት ውል ውስጥ ተሳታፊ የሆኑትን ተዋንያን ለማቀራረብ ጥረት ማድረግ፣ መደገፍና ቀጣይነት ያለው የግብይት ሰንሰለት እንዲፈጠር መስራት፤
- ✓ በተፈጥሮ አደጋ ለሚከሰት ችግር የመድን ሥርዓት ላይ መሳተፍ፤
- ✓ የቡድን አደረጃጀትን መደገፍ፤

### 12.5. የክልል ግብርና ቢሮ

- ✓ በተዋንያን (በአምራችና በአስመራች) መካከል የሚፈፀመው ውል በግብርና ምርት ውል አዋጅ ቁጥር 1289/2015 መመሪያና ደንብ መሰረት መሆኑን ማረጋገጥና መከታተል፤
- ✓ በየደረጃው ላሉ የግብርና ውል ተዋናዮች ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣ ክትትልና ግምገማ ማድረግና ምርጥ ተሞክሮ መቀመር፣ማጠናቀርና ማስፋት፤እንዲሁም ስራዎችን ለማስፈፀም የሚረዳ ስርዓት መዘርጋት፤
- ✓ የግብርና ማምረቱ ሂደት በውሉ መሰረት መካሄዱን መከታተል፤
- ✓ በሀገሪቱ ያለውን የግብርና ምርት እምቅ ሀብትና እድሎችን

በዲጂታልይዜሽን የመረጃ ስርዓት በመያዝ ተደራሽ ማድረግ፣

- ✓ የግብርና ምርት ውል ተሳታፊ አስመራቾችና አምራቾች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መስጠት፤
- ✓ የግብርና ምርት ውል ትስስር በማስፋት ሌሎችንም አስመራችና አምራቾችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማነሳሳትና በመደገፍ ቀጣይነቱን ማረጋገጥ፤
- ✓ የመሰረተ ልማት አውታሮች ማሟላት
- ✓ አለመግባባቶች ቢፈጠሩ በሕግ አግባብ እንዲፈቱ ማመቻቸት
- ✓ ያለመግባባቶችን ምንጭና ሁኔታ በማጥናት በማደራጀት ለቀጣይ ስራ ችግሮቹ እንዳይፈጠሩ የምክረ ሃሳብ ያቀርባለል ::
- ✓ ለግብርና ምርት ውል አካባቢዎች የኤክስቴንሽን አገልግሎት መዘርጋት፤
- ✓ በግብርና ምርት ውል ተዋንየያን የአካባቢ ጥበቃ ላይ ትኩረት እንዲሰጡ መከታተል እና መደገፍ ፤
- ✓ የግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች ለግብርና ምርት ውል ተዋንያን ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ፤
- ✓ የምርምር ተቋማት ለግብርና ምርት ውል አካባቢዎች የሚሆኑ የተሻሻሉ አዳዲስ ዝርያዎችንና ቴክኖሎጂዎችን በማውጣት በኩል ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ፤
- ✓ የኢንሹራንስ የዋስትና መብት ያላቸውን አምራቾችና አስመራቾች በሚገጥማቸው የአደጋ ጊዜ የማካካሻ ዋስትናቸው የተረጋገጠ መሆኑን

መከታተል፡፡

- ✓ የተፈጥሮ አደጋዎች እንደ ጎርፍ የመሬት መንሸራተት የተባይ ክስተት የመሳሰሉትን የመከላከል ስራዎችን ማከናወን፣ አደጋዎች ይመዘግባል፣ መረጃ ያደራጃል፣ ሪፖርት ያደርጋል፡፡
- ✓ የአምራቾችን የግብርና ምርት የማምረትና ጥራት ላይ ክህሎትና አቅምን ለማሳደግ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን፣ መደገፍ፤
- ✓ በቡድን አደረጃጀት ሂደት ድጋፍ መስጠት፤
- ✓ በግብርና ምርት ውል መረጃ አደራጅቶ መያዝ፣ ጠቅላላ የአሰራር ስርዓቱን መከታተል እና ለሚለከተው አካል ሪፖርት ማቅረብ፡፡
- ✓ አስገዳጅ ሰብሎችን በተመለከተ የግብርና ምርት ውል የያዙ የአስመራቾችን ዝርዝር ውሉ እንደተጠናቀቀ የተጠቃለለ ሪፖርት ለንግድና ገበያ ልማት ማሳወቅ አለበት፡፡
- ✓ በግብርና ውል ስምምነት የተመረተውን አስገዳጅ ሰብል ምርት መጠን ለንግድና ገበያ ልማት ማሳወቅ አለበት፡፡
- ✓ በውል ግብርና ለተሰማሩ አምራች ህብረት ስራ ማህበራት፣ ባለሀብቶች እና አርሶአደሮች ግብዓት፣ብድር እና ልዩ ልዩ ቴክኖሎጅዎች እንዲቀርቡላቸው ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡
- ✓ ከግብርና ውል ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ ያስተባብራል ይገመግማል፤ ይደግፋል፡፡

## 12.6. በወረዳ ግብርና ጽ/ቤት

- ✓ በተዋንያን (በአምራችና በአስመራች) መካከል የሚፈፀመው ውል

በግብርና ምርት ውል አዋጅ ቁጥር 1289/2015 መመሪያና ደንብ መሰረት መሆኑን ማረጋገጥና መከታተል፤

- ✓ በየደረጃው ላሉ የግብርና ውል ተዋናዮች ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣ ክትትልና ግምገማ ማድረግና ምርጥ ተሞክሮ መቀመር፣ማጠናቀርና ማስፋት እንዲሁም ስራዎችን ለመተግበር የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፤
- ✓ የግብርና ማምረቱ ሂደት በውሉ መሰረት መካሄዱን መከታተል፤
- ✓ በሀገሪቱ ያለውን የግብርና ምርት እምቅ ሀብትና እድሎችን በዲጂታልይዜሽን የመረጃ ስርዓት በመያዝ ተደራሽ ማድረግ፣
- ✓ የግብርና ምርት ውል ትስስር በማስፋት ሌሎችንም አስመራችና አምራቾችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማነሳሳትና በመደገፍ ቀጣይነቱን ማረጋገጥ፤
- ✓ በግብርና ምርት ውል ተሳተፊ የሚሆኑ አርሶ/አርብቶ አደሮችን በየቀበሌውና በየምርት አይነት በመለየት መረጃ ያጠናቅራል፣ ያቅዳል፣ ለሚመለከተው ክፍል መረጃዎችን ያስተላልፋል፤
- ✓ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን አርሶ/አርብቶ አደሮችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- ✓ በአካባቢው ያሉ አምራቾችን ከአስመራቹ ጋር ማስተሳሰር፤
- ✓ የመሰረተ ልማት አውታሮች ማሟላት ወይም እንዲሟሉ ጥረት ማድረግ
- ✓ አለመግባባቶች ቢፈጠሩ በሕግ አግባብ እንዲፈቱ ማመቻቸት
- ✓ ያለመግባባቶችን ምንጭና ሁኔታ በማጥናት በማደራጀት ለቀጣይ ስራ ችግሮቹ እንዳይፈጠሩ የምክረ ሃሳብ ያቀርባል ።

- ✓ ለግብርና ምርት ውል አካባቢዎች የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፤
- ✓ በግብርና ምርት ውል ተዋንያን የአካባቢ ጥበቃ ላይ ትኩረት እንዲሰጡ መከታተል እና መደገፍ ፤
- ✓ የግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች ለግብርና ምርት ውል ተዋንያን ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ፤
- ✓ የኢንሹራንስ የዋስትና መብት ያላቸውን አምራቾችና አስመራቾች በሚገጥማቸው የአደጋ ጊዜ የማካካሻ ዋስትናቸው የተረጋገጠ መሆኑን መከታተል።
- ✓ የተፈጥሮ አደጋዎች እንደ ጎርፍ የመሬት መንሸራተት የተባይ ክስተት የመሳሰሉትን የመከላከል ስራ ያከናነውናል፣ አደጋዎች ይመዘግባል፣ መረጃ ያደራጃል፣ ሪፖርት ያደርጋል
- ✓ የአምራቾችን የግብርና ምርት የማምረትና ጥራት ላይ ክህሎትና አቅምን ለማሳደግ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን፣ መደገፍ፤
- • በፍላጎት ላይ ተመሰረተ ግብርና ምርት ውል ተሳታፊ አርሶ/አርብቶ አደሮችን በቡድን ማደራጀት እንዲሁም የኩታ ገጠም እርሻ የአሰራር ስርዓትን ለግብርና ምርት ውል አሰራር ስርዓት እንዲጠቀሙ ማስቻል
- ✓ የግብርና ምርት ውል በአስመራችና አምራቾች መካከል እንዲተገበር ቅድመ-ሁኔታዎችን ያመቻቻል።
- ✓ በተዋዋይ ወገኖች የግብርና ውል ስምምነት ሲፈራረሙ እማኝ ሆኖ ያፈራርማል።

- ✓ በተዋዋይ ወገኖች አለመግባባቶች ቢኖሩ በማወያየት ችግሮች እንዲፈቱ ያደረጋል፡፡
- ✓ በግብርና ምርት ውል የሚመረት ምርት መረጃ ማጠናቀር ጠቅላላ የአሰራር ስርዓቱን መከታተል እና ለሚለከተው አካል ሪፖርት ማቅረብ

## 13. የክትትል፣ ድጋፍና መማማር ሥርዓት፤

የግብርና ምርት ውል የአሰራር ስርዓት ውስጥ ቅንጅታዊ የክትትል ሥርዓት በመዘርጋትና ትኩረት ሰጥቶ በማከናወን የግብርና ምርት ውል ተግባርን ውጤታማነት ያጎላል፡፡ የክትትል ስርዓት በአሰራር ላይ ያልተጠበቁ ልዩነቶች ቢፈጠሩ የግብርና ምርት ውሉን ማስተካከልና የሚጠቀሙበትን ቴክኖሎጂ ማሻሻል ወይም ሌሎች ተግባራት ቢኖር በወቅቱ ተገኝቶ ለማስተካከል ጠቃሚ ነው፡፡

### 13.1. ምርታመነትን እና የምርት ጥራትን መከታተል

ምርታማነትን እና የምርት ጥራትን ለማረጋገጥ በክትትል ወቅት የሚከተሉት ተግባራት መከናወን አለባቸው፡፡

- የማሳ ዝግጅትን አስመልክቶ እንደ ግብርና ምርት ዓይነቱ እና ባህሪ መዘጋጀቱን መከታተል
- በዘር ወቅት ማሳው መለካቱን፣ተገቢው ግብዓት መቅረቡንና ጥቅም ላይ መዋሉን፤
- በሰብሉ የዕድገት ሂደት በአግባቡ እያረመ፤ የተባይ መከላከል ስራ እየሰራ መሆኑን፤
- ምርቱ ከመድረሱ በፊት የምርት ግምት (ቅድመ ምርት ትንበያ

በአግባቡ መከናወኑን፤የፓኬጂንግ ቁሳቁሶች ማዘጋጀትን፤

- በምርት አሰባሰብ ወቅት የምርት ብክነት የጥራት መጓደል እንዳይከሰት ጥንቃቄ እየተደረገ መሆኑን፤
- ምርቱ ከተሰበሰበ በኋላ በአግባቡ መከማቸቱን፤
- ህጋዊ ፍቃድ የሌላቸው  ደላሎችን መቆጣጠር፤
- በውል ስምምነቱ መሰረት ግብዓትና ፋይናንስ መቅረቡን፤
- ክፍያዎች በውሉ መሰረት መከናወናቸውን፤

እና ሌሎች የአመራረት ሁኔታዎች /Production matrix/ በመለየት ወቅታዊ ክትትል ማድረግ ይገባል።

### 13.2. የሰው ሃብት ክትትል

በግብርና ምርት ውል ከተሰማራው ጋር ጠንካራ የሆነ ግንኙነት መፍጠር ሊከሰት የሚችል አደጋን ሊቀንስ ይችላል። በክትትል ወቅት የታቀዱ ተግባራት ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ የሰው ሃብት አጠቃቀምን አስመልክቶ ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ክትትል መደረግ ይኖርበታል፤ ከእነዚህም መካከል

- ✓ የአስመራቹን የኤክስቴንሽን ሰራተኞችና የአምራቹን ግንኙነት ማየት፤
- ✓ በአመራረቱ አሰራር ላይ ባለሙያዎቹ ያላቸውን ዕውቀት መገምገም፤
- ✓ የባለሙያዎች የጉብኝት ድግግሞሽና የምክር አሰጣጥ ይዘት ማጥናት፤
- ✓ ሁሉም የመስክ እንቅስቃሴዎች ዝርዝር ተግባራት ከተከናወኑበት ቀን ጭምር ባበለሙያዎችና በምክር ተጠቃሚዎች በሰነድ ስለመያዙ ማረጋገጥ

በአጠቃላይ ተግባራዊ በሚሆኑ ወቅታዊ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ወቅት አምራቹ በሚሰራቸው ስራዎች ላይ የሚታዩ ችግሮች በመስክ በመለየት፣የአቅም ግንባታ ስራዎችን ተከታታይነት ባለው መልኩ በመስጠት ችግሮች የሚፈቱበትን ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይገባል፡፡ ይህንም በተለይ በትስስሩ የተሳተፉ የማህበራት/የዩኒየን አመራሮች ስራቸውን በእውቀት መስራት የሚያስችል የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የስልጠናና የትምህርት እድል የሚያገኙበትን ሂደት በእቅድ አቅዶ በመንቀሳቀስ የአምራቹን አሰራር በማዘመን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ ይቻላል፡፡

ይህንን ተሳትፏዊ የክትትል፣ ድጋፍና የመማማር ስርዓት በመዘርጋት የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣና ችግሮች ሲያጋጥሙ ወቅታዊ የመፍትሄ እርምጃ ለመውሰድ የሚረዳ ድልድይ እንዲፈጠር ያስችላል፡፡

**የውል-ሰነድ**

የግብርና ምርት ውል በሁለት ወገኖች መካከል የሚፈፀም የማምረት፣የመሸጥና የመግዛት/ የውል ስምምነት ነው፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **ተዋዋይ ወገኖች**

ይህ ውል በ-------------------------- የግል ባለሃብት/ ፋብሪካ/ካምፓኒ ከዚህ በኋላ ድርጅት ተብሎ የሚጠራው በአንድ በኩል እና በሌላ በኩል -------- --------------- በግብርና ምርት ውል ውስጥ የተሳተፉ አምራች/አምራቾች ማህበር/ዩኒየን/ኃ/የተ/የግ/ማ/ ከዚህ በኋላ አምራች/ማህበር/ዩኒየን/ኃ/የተ/የግ/ማ/ ተብሎ የሚጠራ በሌላኛው ወገን ሆኖ/ሆነን ዛሬ በ--------------------- ዓ.ም ከማናቸውም ተፅዕኖ ነፃ በሆነ ሁኔታ ፈቅደንና ተስማምተን በፍትሃብሔር ሕግ ቁጥር --------------------------- በተደነገገው መሰረት ያደረግነው የውል ስምምነት መሆኑን በማረጋገጥ ተስማምተን ፈርመናል፡፡

1. **ቋሚ አድራሻ**

ለዚህ ውል አፈፃፀም ሲባል የተዋዋይ ወገኖች ቋሚ አድራሻዎች የሚከተለው ይሆናል፡፡

የአስመራች ስምና አድራሻ፡-

የ------------------------------------- የግል ባለሃብት/ፋብሪካ / ካምፓኒ ክልል--- -----------ዞን--------------------ወረዳ-----------------ቀበሌ-----------------የቤት ቁጥር-------------------- ስልክ ቁጥር--------------------ኢ.ሜል ----------------

-------- የንግድ ፍቃድ ቁጥር ..............................

የአምራች ስምና አድራሻ፡-

የ------------------------- አምራች/አምራቾች ማህበር/ዩኒየን ክልል------------

-----------ዞን------------------ወረዳ-----------------ቀበሌ ገበሬ ማሕበር--------

---------------- ስልክ ቁጥር---------------- ፖስታ ሳጥን ቁጥር--------------

ኢ.ሜል ------------------------

## 2. የውል ዘመን

ለተዋዋይ ወገኖች የጋራ ጥቅም ሲባል በሁለቱም ወገኖች ስምምነት ወይም በሕግ ወይም ከዚህ ውጭ በተጠቀሰ ምክንያት የ-----------------ጊዜ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተቀባብለው ተዋዋይ ወገኖች ካላቋረጡ በስተቀር በሁለትዮሽ የጋራ ስምምነት ባስቀመጡት መሰረት ይህ ውል ላልተወሰነ ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፡፡

## 3. የውሉ ቋንቋ

የዚህ ውል አፈፃፀም የሚመለከቱ ጉዳዮችና የጽሁፍ ግንኙነቶች በሙሉ የሚከናወኑበት የክልሉ ሥራ ቋንቋ ሆኖ በተጨማሪም በብሔራዊ የሥራ ቋንቋ እንዲዘጋጅ በስም የተጠቀስነው ተዋዋይ ወገኖች የተስማማን ሲሆን ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ተወካዮችና እማኞች በተገኙበት ከተፈራረሙ በኋላ ቅጂው በሁለቱ ተዋዋዮችና በሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ዘንድ ይቀመጣል፡፡_

## 4. አለመግባባትን ስለመፍታት

ከዚህ ውል አፈፃፀም ጋር ተያይዘው በሚነሱ ማንኛውም አይነት አለመግባባቶች ሁለቱም ወገኖች በውይይት ለመፍታት ተስማምተዋል፡፡ የተፈጠረው አለመግባባት በስምምነት ካላለቀ ማንኛውም ወገን በሕግ የመጠቀም መብቱ

እንደተጠበቀ ነው። ስለዚህም ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች አጋጥሞኛል የሚለው ወገን ስለሁኔታው ባወቀ በ----------ቀናት ውስጥ ለሌላኛው ወገን የማሳወቅ ግዴታ አለበት። በመሆኑም ለዚህ ውል አፈፃፀምና አተረጓጎም ሲባል የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግና አግባብነት ያለው የፌደራልና የክልል መንግስት ሕግ ተፈፃሚነት አላቸው።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

### <u>የውሉ ዓላማና ዝርዝር አፈፃፀም</u>

### 5. <u>የውሉ ዓላማ</u>

የ------------------------ የግል ባለሃብት/ ፋብሪካ/ ካምፓኒ በውላቸው መሰረት ከአምራቹ /ከማህበሩ ወይም ከዩኒየኑ የሚያመርቱትን ምርት ለመግዛት ፈቃደኛ መሆኑን ገልጦ ስላረጋገጠ። እንዲሁም አምራቹ/የአምራቾቹ ማህበር/ ዩኒየኑ በበኩሉ በተፈለገው የምርት ዓይነት፣ መጠን እና ጥራት ደረጃ በጋራ በተስማሙበት መሰረት ሊያቀርብለት እንደሚችል ፈቃደኝነቱን ስላረጋገጠ፤ ከዚህ በላይ በክፍል አንድ ስር በስም የተጠቀስነው ይህን ውል ተግባራዊ ለማድረግ መስማማታችንን እናረጋግጣለን።በ---------------------ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በ-----------------ዞን

በ-----------------ወረዳ ------------- ቀበሌ ------------- ውስጥ ለ-------------
---------ልማት በተመረጡ ------------------ ንኡስ መንደሮች የማሳ አዋሳኞች ………………………………………… የሚለማ ምርት በአምራቹ/በአምራቾቹ ማህበር/በዩኒየኑ አማካይነት ለ-------------------- የግል ባለሃብት/ ፋብሪካ/ ካምፓኒ በማቅረብ ተጠቃሚ መሆን፤

## 7. የውሉ ዝርዝር አፈፃፀም

1. የሚለማው/የሚመረተው/የሚዘጋጀው ምርት፣ የሚለማው መሬት ላይ ለሰብሉ ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ ደባል የሰብል ዝርያዎች የሚመረቱ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ የመሬቱን ምርታማነት ለመጠበቅ የሚችሉ የተለያዩ የአፈር ጥበቃ ሥራዎች የሚከናወኑ ይሆናል።
2. በውል ግብርና ሥርዓቱ የተጠቀሰው ሥራ አተገባበር፤በውሉ ውስጥ የተጠቀሰው ተግባር የሚከናወነው መሰረታዊና ዘመናዊ የሆነ አመራረት ዘዴን በመከተል ይሆናል።
3. የጋራ አሰራር ስምምነት: የሚፈለገውን ምርት መጠንና አይነት በማምረት ሂደት በቅርበት ለአምራቹ/ በአምራቾቹ ማህበር/ በዩኒየኑ/ ፋብሪካ/ የግልባለሃብት/ ካምፓኒ የሚሆን ምርት አስቀድሞ ከፋብሪካ/ ከግል ባለሃብት/ከካምፓኒው ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሰረት በወጡ መስፈርቶችና መርሃ-ግብር እንዲመረት የአምራቹ/የአምራቾቹ የማህበሩ/ የዩኒየኑ አስፈፃሚ አካል የመከታተል ሀላፊነት አለበት።
4. የግብዓት አቅርቦትን፣ ምርት መጠን፣ ግብይት ቦታና የማጓጓዣ ወጪ በተመለከተ ተዋዋዮች በሚስማሙበት ሁኔታ ግልፅ ሆኖ መቀመጥ አለበት

## ክፍል ሶስት

<u>የተዋዋዮች ኃላፊነትና ግዴታ</u>

- የግል ባለሃብቱ / የፋብሪካው/ የካምፓኒው ኃላፊነትና ግዴታ:-

1. አምራቹ/የአምራቾቹ ማህበር/ዩኒየኑ እና የግል ባለሃብቱ /ፋብሪካው/

ካምፓኒው በተስማሙትና የወቅቱን ዋጋ ባገናዘበ መንገድ ምርቱን ለማቅረብ በተያዘው ምክረ-ሃሳብ፣ መርሃ-ግብርና ጊዜ ምርቱን ይገዛል። ይህም ዋጋ እንዳስፈላጊነቱ በተወሰነ ጊዜ በሁለቱም ወገኖች ስምምነት ሊለዋወጥ ይችላል።

2. ቀደም ብሎ አምራቹ/አምራቾቹ ማህበሩ/ ዩኒየኑ እና ፋብሪካው /የግል ባለሃብቱ /ካምፓኒው በጋራ በሚያወጡት ፕሮግራም መሰረት ፋብሪካው / የግል ባለሃብቱ/ ካምፓኒው ግብዓቶችንና የድጋፍ አገልግሎቶችን አዘጋጅቶ ለአምራቹ/ለአምራቾቹ ማህበር/ለዩኒየኑ በማሳወቅ ያቀርባል።
3. በመርሃ-ግብሩ መሰረት የሚቀርበውን ደረጃውን የጠበቀ ምርት በወቅቱ በመረከብ ግልፅ የሆነ የመተማመኛ ሰነድ የመስጠትና በስምምነቱ መሰረት በተገቢው ወቅት ክፍያ ይፈፅማል።
4. ሁለቱ ወገኖች በተዋዋሉት መሰረት የመቀባበል ሥርዓት እያለ የጎንዮሽ ሽያጭ ከተካሄደ አምራቹን በሕግ አግባብ ተጠያቂ ማድረግ።
5. የግል ባለሃብቱ፣ፋብሪካው፣ካምፓኒው፣ አምራቹ በወቅቱ የሰበሰበውን ምርት በውሉ መሰረት ካልተረከበ እና የመረከቢያ ጊዜን ካራዘመና መረከብ ካልቻለ ------- በመቶ (%) ጨምሮ ምርቱን የመረከብ ግዴታ አለበት።

➢ **የአምራቹ/አምራቾቹ ማህበር/ዩኒየኑ ኃላፊነትና ግዴታ:**

1. በጋራ ስምምነት መሰረት አስቀድሞ በሚወጣ ምርት ደረጃና ጥራት የተመረተ ምርት በትክክለኛው ጊዜና ሰዓት ለፋብሪካው/ ለግል ባለሃብቱ/ ለካምፓኒው ያቀርባል።
2. በግብርና ምር ውል ያመረታቸውን ምርቶች ለፋብሪካው/ለግል ባለሃብቱ/ ለካምፓኒው ብቻ ይሸጣል።

3. በፋብሪካው/በግል ባለሃብቱ/በካምፓኒው የተዘጋጁትን ግብዓቶችና አገልግሎቶች በወጣው ፕሮግራምና በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ይወስዳል/ በምክረ-ሃሳቡ መሰረት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤ ይፈጽማል።
4. በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አምራቹ/አምራቾቹ ማህበሩ/ ዩኒየኑ በፋብሪካው/ በግል ባለሃብቱ/ በካምፓኒው የተዘጋጁትን ግብዓቶች በውሉ መሰረት ማንሳት ካልቻለ በዝግጅት ምክንያት ለባከነው ምርት ተመጣጣኝ የዋጋ ተጠያቂ ይሆናል።

## ክፍል አራት

### የግብይት ሥርዓት:-

የፋብሪካ/ ግል ባለሃብት/ ካምፓኒ የሚቀርብለትን ምርት የወቅቱን የማምረቻ ዋጋንና የምርት መሸጫ የገበያ ዋጋን ባገናዘበ መልኩ የተሰሉ የመግዣ ዋጋዎች ለአምራቹ/ለአምራቾቹ ለማህበሩ/ለዩኒየኑ ሥራ አስፈፃሚ በየጊዜው ያሳውቃል። ይህም ስሌት እንደ አስፈላጊነቱ በምርቱ አቅርቦት የቆይታ ጊዜ መሰረት የሚሰላ ይሆናል ።

በመጀመሪያው ለመነሻ የሚሆን ለሚቀርብለት ምርት ለእያንዳንዱ ኪሎ ግራም በወቅቱ ገበያ ላይ ---- መቶኛ በመጨመር ለመክፈል ተስማምቷል።

## ክፍል አምስት

### ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች /አባሪ/

1. ውሉን የመፈፀም ግዴታ:-

ተዋዋይ ወገኖች በፍ/ሕ/ቁ. -------- መሰረት እና በዚህ በተቀመጡት ውል

በፎርሙ ላይ የተጠቀሱትን አንቀፆች በሙሉ ሳይሸራርፉ ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለባቸው። አንዳቸው የግዴታው ተገዢ ካለመሆናቸው የተነሳ ለሚደርሰው ጉዳትና ኪሳራ የሚመለከተው ወገን በውሉ መሰረት በፍትሐብሔር ሕግ ተጠያቂ መሆኑ ተጠብቆ የውሉ ተፈፃሚነት ሳይቋረጥ ይቀጥላል።

የፋብሪካ /ግል ባለሃብት/ ካምፓኒ ከአቅም በላይ በሆነ የቴክኒክ ችግር ምክንያት የምርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪው ጊዜያዊ የሥራ መስተጓጎል ቢያጋጥመው ሁኔታውን ቀድሞ ለአምራቹ /ለአምራቾቹ ለማህበሩ/ ለዩኒየኑ ሊያሳውቅ ይገባዋል። አምራቹ /አምራቾቹ ማህበሩ/ ዩኒየኑ ችግሮቹ በተፈጠሩበት ወቅት ምርቱን ለአማራጭ ገበያዎች ማቅረቡ እንደተጠበቀ ሆኖ አምራቹ ሊያገኝ ይችል የነበረውን ተጨማሪ ጥቅም ኪሳራ ሁለቱም አካላት ሊካፈሉት ይገባል።

## 2. አስማሚ አካል ስለማቋቋም:-

በተዋዋይ ወገኖች የሚከሰቱ ችግሮችን በተመለከተ መፍትሄ የሚሰጥ በጋራ የሚያቋቁሙት አስማሚ አካል ሊኖር የሚገባ ሲሆን ጉዳዩ ከዚህ አካል አቅም በላይ ከሆነ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ጉዳዩ እንዲታይ ማድረግ ይችላል።

## 3. ውል ስለሚቋረጥበት ሁኔታ:

በዚህ ውል ላይ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ሳይፈፀም ውሉን በተናጠል ለማፍረስ የሚሞክር ወገን ቢኖር በሌላኛው ወገን ለሚደርሰው ኪሳራ ተጠያቂ ይሆናል። ወይም ይህ ውል መቋረጥ የሚችለው ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በስምምነት ፍቃደኛ ሲሆኑ ወይም ውሉ ሊቋረጥ የሚችለው የውል ዘመኑ ሲያልቅ ወይም እንዲራዘም ስምምነት ካልተደረገ ሊቋረጥ ይችላል።

## 4. ውል ስለማሻሻል:-

ተዋዋይ ወገኖች የውል ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት የውሉን ድንጋጌዎች ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ ከተስማሙ ውሉን በማንኛውም ጊዜ በጽሁፍ ሊያሻሽሉት ይችላሉ፡፡

ውሉ ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን: ይህ ውል ከ--------- ቀን------------- ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

1. ውሉ የተፈረመበት ቦታና ቀን:

ይህ ውል በ----------------------ቦታ በ-----------------ቀን ----------------ዓ.ም በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ተፈረመ፡፡

2. ውሉ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ:

ይህ ውል ከተፈረመበት ከ------------------------ ጊዜ ጀምሮ አምራቹ ምርቱን ሰብስቦ ለባለሀብቱ/ፋብሪካው/ኩባንያው እስከ ሚያስገባና ሂሳቡን እስከሚረከብ ድረስ ፀንቶ ይቆያል፡፡

ይህ ውል ዛሬ ----------------------------ቀን ----------------ዓ.ም ------------------- ከተማ በሶስት ምስክሮች ፊት ተፈረመ፡፡ ውሉም ሕጋዊነት እንዲኖረው አግባብ ባለው የአቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት ቀርቦ አርሶአደሩ/አምራቾች ማህበሩ/ ዩኒየኑና ፋብሪካው/የግል ባለሃብቱ/ካምፓኒው እንዲሁም እማኞች በውሉ ላይ በሚያሰፍሩት ፊርማ የውሉ ሕጋዊነት ይረጋገጣል፡፡

3. <u>የተዋዋይ ወገኖች ፊርማ</u>

<u>ስለአምራቹ/አምራቾቹ ማህበር/ ዩኒየን</u>

የ---------------------------------------- አምራች/አምራቾች/ማህበር/ዩኒየን

በ--------------------ክልል፣በ--------------------ዞን፣በ--------------ወረዳ፣በ---

-----------------ቀ/ገ/ማ፣ሥም--------------------------------------

ፊርማ---------------------------------ቀን----------------------------

የ-------------------- ፋብሪካው/ የግልባለሃብቱ/ ካምፓኒው _

በ--------------------ክልል፣በ--------------------ዞን፣በ--------------ወረዳ፣ በ--------
------------ቀ/ገ/ማ፣ሥም--------------------------------------ፊርማ-----

----------------------------ቀን----------------------------

## 4. <u>ውሉ ሲፈረም የነበሩ /እማኞች</u>

ከዚህ በታች ስማችን የተዘረዘረው እማኞች ሁለቱ ወገኖች አርሶአደሩ/ አምራች ማህበሩ /ዩኒየኑና ፋብሪካው/የግል ባለሃብቱ/ካምፓኒው/ በዚህ ውል የተደነገጉትን ኃላፊነትና ግዴታዎች ለመፈፀም ተስማምተው ሲፈራረሙ ተገኝተን የተመለከትን መሆናችንን በፊርማችን እናረጋግጣለን።

1. ሥም---------------አድራሻ -------------ፊርማ -------------ቀን-------
2. ሥም---------------አድራሻ -------------ፊርማ -------------ቀን--------
3. ሥም---------------አድራሻ -------------ፊርማ -------------ቀን--------
4. የሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት / ድርጅት

ሥም---------------አድራሻ -------------ፊርማ -------------ቀን-------

## ዋቢ መጻህፍት/ሰነዶች

1. Country Experience on Implementation of Out-growers Scheme, Ethiopian Horticulture Development Agency (EHDA), May, 2014

2. Contract Farming Notes, Local and International Experience on Contract farming_and oil seeds in Humera, Contract Farming and business arrangement Experiences , Experiences sharing on family milk Contract arrangement ,Success and challenges of Contractual arrangement with identified out-growers. April ,2010_

3. Contract farming Partnerships for growth, by Charles Eaton and Andrew W. Shepherd, 2001

4. IMPACT OF CONTRACT FARMING ON SMALLHOLDER POULTRY FARMERS' INCOME IN KENYA by Priscilla W. Wainaina, Julius J. Okello & Jonathan Nzuma, August, 2012

1. THE STATUS OF CONTRACT FARMING AND CONTRACTUAL ARRANGEMENTS IN ZAMBIAN AGRICULTURE AND AGRIBUSINESS BY 12.2.ክልል ግብርና ቢሮዎች

5. MWIKISA L. LIKULUNGA, Decmber, 2005

6. Sensitization Training On Development of Out-grower Scheme Ethiopia Horticulture Development Agency, June, 2016

7. Country Experience on Implementation of Out-growers

Scheme, Ethiopian Horticulture Development Agency (EHDA), May, 2014

8. Contract Farming Legal framework-update and inputs on the draft document, Ethiopia transformation Agency, April, 2017

9. በኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የቡና ልማትና ግብይት ትስስር / Out-growers Scheme/ የአሠራር ስርአት, ግንቦት, 2009

10. ኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለስልጣን የሁለተኛው ዕትዕ ቀጣይ ሶስት አመታት, ሰኔ, 2010

11. የግብርና ምርት ግብይት በኮንትራት ውል የሚፈጸም የአውትግሮወርስ ስርአት (outgrowers contrat farming) የአፈጻጸም መመሪያ፣ ግብርና ሚ/ር, ህዳር, 2003

12. የግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አጠቃቀም ማሻሻያ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች አፈጻጸም መመሪያ, የኢትዮጵያ ግብርና ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ, ሰኔ, 2004

ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

Co-funded by the European Union

german
cooperation
DEUTSCHE ZUSAMMENARBEIT

Implemented by
giz Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) GmbH



10
ኃላፊነት የተሞላበት የግብርና ኢንቨስትመንት መርሆዎች
Responsible Agricultural Investment (RAI) Principles
01
ለምግብ ዋስትና እና የተመጣጠነ ምግብ መሻሻል አስተዋጽኦ ማድረግ
Contribute to food security and nutrition
› የተለያዩ ባህላዊ፣ ደህንነታችው የተጠበቀና በአልሚ ንጥረ ነገሮች የበለጸጉ ምግቦችን ማምረት
› አነስተኛ አምራቾችን ለመደገፍ ገበያን ማስፋት
02
ዘላቂ እና አካታች የኢኮኖሚ ልማትን እና ድህነት ቅነሳን ማገዝ
Contribute to sustainable and inclusive economic development and the eradication of poverty
› የህጻናት ጉልበት ብዝበዛን ማስወገድ
› ለተሻለ ውጤት የተሻለ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት
03
የጾታ እኩልነት እና የሴቶችን አቅም ማጎልበት
Foster gender equality and women's empowerment
› ሥራ የመሥራት መብትን ማክበር
› የመሬት ይዞታ ባለቤትነት መብትን ማክበር
04
ወጣቶችን ማሳተፍና ማብቃት
Engage and empower youth
› በተፈጥሮ ሀብት የመጠቀም እና የመደገፍ መብት ማክበር
05
የመሬት፣ ዓሣ እና ደን ሀብት ይዞታ መብትን እና የውሃ ተደራሽነትን ማክበርና ማረጋገጥ
Respect tenure of land, fisheries and forests and access to water
› የአካባቢ ማህበረሰብን በየደረጃው ማማከርና ማሳተፍ
› የአነስተኛ አርሶ አደሮችን ምርታማነት ማሳደግ
06
የተፈጥሮ ሀብትን በመጠበቅና ዘላቂ በሆነ መልኩ በማስተዳደር አይበገሬነትን ማጠናከርና የአደጋ ተጋላጭነትን መቀነስ
Conserve and sustainably manage natural resources, increase resilience, and reduce disaster risks
› የብዝሀ ሕይወትና ዘረመል ሀብቶችን መንከባከብና መጠበቅ
› ቴክኖሎጂን ማላመድ፤ የድህረ ምርት ብክነትንና ብልሽትን መቀነስ
› የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን መቀነስ/ማስወገድ
07
ባህላዊ ቅርሶችንና አካባቢያዊ እውቀቶችን ማክበር እና ብዝሃነትንና ፈጠራን መደገፍ
Respect cultural heritage and traditional knowledge, and support diversity and innovation
› ጥንታዊ ቅርሶችንና ባህላዊ ሥርዓቶችን ማክበር
› ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር በተግባቦትና በመከባበር መሥራት
› በአካባቢው የተላመዱ ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን ማስፋፋት
08
ደህንነቱ የተጠበቀና ጤናማ የሆነ ግብርና እና የምግብ ሥርዓት መዘርጋት
Promote safe and healthy agriculture and food systems
› የእንሥሣት ጤና ጥበቃን መደገፍ
› የምግብ ደህነትን ለመቆጣጠር ሳይንሳዊ ዘዴዎችን መጠቀም
09
አካታችና ግልጽ የሆነ የአስተዳደር መዋቅር፣ የሥራ ሂደት እና የግጭት አፈታት ሥርዓት መዘርጋት
Incorporate inclusive and transparent governance structures, processes, and grievance mechanisms
› ከሙስና የጸዳ አሰራር
› የመረጃ ግልጸኝነትና ለአካባቢው ማህበረሰብ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ
10
አሉታዊ ተጽዕኖዎችን መለየት፣ መፍታትና ተጠያቂነትን ማስፈን
Assess and address impacts and promote accountability
› መረጃዎችን በማሰባሰብ በመተንተን አሉታዊ ተጽዕኖዎችን እና መፍትሄዎቻቸውን መለየትና ለባለድርሻዎች ማሳወቅ
Co-funded by the European Union
german cooperation
DEUTSCHE ZUSAMMENARBEIT
Implemented by
giz
MINISTRY OF AGRICULTURE